
# የብርሃን ፍቅር

ከደበበ ሰይፉ



NIGUSS DIGITAL LIBRARY

# የብርሃን ፍቅር

ቅጽ ፩

ከደበበ ሠይፉ

ሥነ ግጥም

፲፱፻፹

# ማውጫ

**ርዕስ ........ ገጽ**

እንደ መነሻ ........ 14

ሙዚቃ - የምች መድኃኒት ........ 17

ተስፋ - ጨረቃ ........ 20

ድንቄም መምህር ........ 22

ብቸኝነት ........ 23

ወፊቱ ........ 23

የሕይወት እጅ ........ 24

ይረጋ ዓለም ........ 25

ሰማይና ምድር ........ 28

ያቺ ቆንጂት ........ 29

እማማ....እማምዬ ........ 32

ዳኢት (አንዲት የሲዳሞ ሴት) ........ 37

አዴ ላንቃሞ (አንድ የሲዳሞ ወንድ) ........ 40

እቴቴ ........ 45

ላንቺ ለጨለማዋቱ ........ 48

ልጅነት ........ 49

ወለምታ (የወዳጅነት አባዜ) ........ 52

ያባትህ ልጅ ........ 53

የንፋግ ምጽዋት ........ 58
አዬ የኔ ዝምታ ጋግርት ........ 60
ልጅቱ - የዘመነችቱ ........ 61
ስንብት ........ 64
ፀሐይን ላያይ ተፈጥሞ ........ 68
ሽር በይበት ሽር ........ 70
ዘመዴን ስስመው ........ 71
አንተን በመኻል አያሳጣኝ ........ 71
አለ፥ ‹ጠና በል› እሚለኝ ........ 73
እሱ ነው - እሱ ........ 75
ዛሬን እንኳን ........ 76
ብቻ መገኘትሽ ........ 79
ሐዘንሽ አመመኝ ........ 80
ለድንገት - በቀል ፈላስማ ዐርበኞች ........ 82
ቋጥኙ ........ 85
በትን ያሻራህ ዘር ........ 86
ትዝታን ማለስለሻ ........ 87
ገና በልጅነት ........ 89
መንታ ነው ፍጥረትሽ ........ 90
የቀበሮ ጉድጓድ ........ 91

ጥሬ ጨው ........ 92
አድማሳዊ ፍቅር ........ 93
መስከረም ........ 94
በስሙ ሠየማት ........ 109
ምነዋ ባየሁኝ ........ 110
ጋዜጣው ........ 111
ትዝታ - ከበሮ ........ 114
ፍቅርና ተግባር (አንድ ቅንጣት አበባ) ........ 115
አይ ጆኒ አይ ጆሊ ........ 117
ያቺ ሚች ቀን ........ 122
ጉዟችን ........ 124
እንደግ እንደ ዛፍ ........ 128

የብርሃን ፍቅር ወይስ የፅልመት ገበና?

«ሲነጣጠል በቀለማት፥ ሲበታተን እንደ ፋና ማን አወቀው - ማንስ ለየው፣ የዛን የፅልመት ገበና?»

(ለራስ የተጻፈው ደብዳቤ)

አንብበን የምንዘነጋው ሳይሆን፥ ከውስጣችን የሚላወስ ግጥም ነው ደበበ ሰይፉ የሚቀኘው። የተወለደው፣ ልጅነቱንም እስከ ስምንተኛ ክፍል ያጣጣመው በይርጋ ዓለም ነበር። ለተፈጥሮ ውበት፥ ለህፃን ጉጉት፥ አፍላ ልቡ የተበተበተላት ከተማ የዕጣዋ መወላገድ ቆጥሮታል። «ዋ.....ይርጋ - ለም..... /አባ ወራው እንደ ሞተበት/ ወራሽ እንዳለማበት/ ገፊ ቤት/ሲያይ ስትዘነጣጢይ/ እሚገጥምሽ ጠፋ ወይ?» ደበበ ለቦታ ብቻ ሳይሆን ለማቀቁት ግለሰብ ሆነ ማኅበረሰብ መንፈሱ ይቃትታል። «የክረምት ማገዶች» ግጥሙ ዘመን ተሻግሮ ዕድሜ ልክ ሰብአዊያን የሚዘምሩት ነው.....ሌላውን የመበደል አባዜ ከሰው ልቦና ያደፈጠ ባህሪ ነውና።

ከጨለጨልንለት የደሃውን፣ ቀዣ ከል ጭራሮ

ካበሰልንለት ዘንድ፣ የአርሶ አደሩን ንፍሮ

ሰርቶ አደሩን ሕዝብ፣ ለሰስ ያለ ሽሮ፣

ታሪክ ይዘምረው የኛን እንጉርጉሮ።

ዘመን ይመስክረው፣ የኛን ውጣውረድ የእንግልት ኑሮ።

ምናልባት እድሜው አስራ አራት ሳለ ነበር ወደ አዲስ አበባ የመጣው። ሌላው ሰላሳ - አርባ ዓመት ከአንድ ስፍራ ኖሮ፥ የምናብ ዝምታ እንጂ ቁጭት ሳይመዘምዘው ያዝግማል። ደበበ ግን በለጋ ዕድሜው ያጤነውን የኖረውን መቀኘቱ ይመስጣል። «ዳኢቴ» «አዴ ላንቃሞ» «ልጅነት»፥ «እቴቴ»......የሴት በደል የወንድ የማንአህሎኝነቱ የሚያሞካሽ ባህል፥ የልጅነት መክሊት፥ የውብ እንስት ትዝታ በዚያ ዕድሜ ከጊዜ የፈለቀቃቸው ክስተቶችና የአዲስ አበባ

ግርግርና ስፋት ያልፋቁት አንድ የጎላዌ ጠገጉ ነበር። ታድያ መዝገብ፣ በዝርው ማሰልቸት ሳይሆን በረቀቀ እምቅ ውብ ቋንቋ ነው የተቀኘው።

'Great Literature is Simply Language Charged With Meaning to the utmost possible degree.' ብሏል ዝነኛው ባለ ቅኔ ዕዝራ ፓውንድ። የላቀ ሥነ ጽሑፍ ምሥጢሩ በተለበለበ ቋንቋ ለትርጓሜ፥ ለአንድምታ መንዘሩ ነው እንደ ማለት። እንዴት? ደበበ የቋንቋው መለብለብ ብቻ ሳይሆን፥ ምስል መከሰቱ ብቻ ሳይገታው፥ ባለ ቅኔ እንኳን የሚስተውን አንዳች ሁነት በምናቡ ያሰግራል። ስለ ገደል ማሚቶ ያፈለቀው እሳቦትና ጥበባዊ ውበት ይነዝራል። «የገደል ማሚቶ ትንቃ፤ ከእቅልፍ ትራሷ ትከንበል/ ከቦዘን ህልሟ ትፈንግል» እያለ በ «ዛሬን እንኳን» ግጥሙ አንደበታቸው ስለዛገ ትውልድ ተለዋጭ ዘይቤ ሆኖታል። «የገደል ማሚቶ አንቀላፍታ፤ ድምፃችሁን ተንተርሳ/ በእሳት ዳር ምን ይውሳ?/ በሊቃውንት ምን ይነሳ?» በ «ሰብአ ትካት» ግጥሙ ከርሞ ጥጃ ለሆነ ሰነፍ ትውልድ»፥ ተቆጭቷል። የገደል ማሚቱን እሳቦትና ግጥሞች ለቅኔው እርሾ ሆነውታል። ይህን የደበበ ልዩ ችሎታ መስፍን ሀብተ ማርያም <u>«ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ»</u> ሲያነብ መግቢያው ላይ ጠቅሶታል። «ጽለ ተፈጥሮ ሲገጥም ፀሐይና ጨረቃ፥ ቀስተ ደመናና የገደል ማሚቶ ያጅቡታል።...... ‹አዋይ›ን ሲያነሳ የማኅበራዊ ህይወት ቋንቋ ያደርጋታል።» ፍልስፍና ነክ፥ የፍቅር ጉዳይ፥ የሀገር ጥያቄ...... ጠነን ያሉ ጭብጦቹ ቢሆኑም የማኅበረሰቡን ትውፊታዊ እምነት ሳያጥላላ ከውስን መቼታቸው አላቀቃቸው። «አዋይ ታቃስተው ይሁን፥ የገደል ማሚቶ ታልቅሰው/ ወይስ አድባር ትጬኸው?» የባለቅኔው ጥያቄ ዛሬም ያስተጋባል። ገጣሚያን ችላ ያሉትን ይህን - አዋይና ገደል ማሚቶ የቋጠሩት - ትውፊታዊ እሴት ደበበ ለመመዘኛ ይህወት ማንፀሪያ አድርጐታል። በተለይም የረቀቀው ገደል ማሚቶን የዘመነኛ ሥነ ተረት። - myth - ሊያሳክል «ባለ አደ» ግጥሙን ተቀኘ።

የገደል ማሚቶ መጣች፣

በዘመን ጭራ ታስራ።

የአእላፍ ሙታን ድምፅ

ቋጥራ።

አደራ።

የደበበ ሰይፉም ሥነ ግጥም አእላፍ ድምፅ የተጠነፈፈበት አደራ ነው። ረዘም ካሉ ግጥሞቹ እንደ «መስከረም፣ «ለራስ የተጻፈድ ደብዳቤ» እና «ከአክሱም ጫፍ አቁማዳ» ጥበባዊ ውበት እና እሴታቸውን ለመፈልቀቅ የጥሞና ጥናት ይሻል። ብርሃኑ ገበየሁ «ዘመናዊ የአማርኛ ሥነ ግጥም፣ አንዳንድ ነጥቦች» በሚለው ወረቀቱ የደረሰበት ሀቅ አለ።

«በአማርኛ ግጥም በቤት አመታት ስልትና በዜማ ከተራቀቁ ገጣሚያን አንዱ ደበበ ሰይፉ ሲሆን......በስነ ግጥማችን ታሪክ ውስጥ ታላቅና ሁነኛ ቦታ ያለው ነው። የደበበ ገጣሚነት ከህዝባዊነት መንፈስ ይመነጫልና ብዙ ጊዜ ታላላቅ አገራዊ ጉዳዮች ኪነ ጥበባዊ ቅርፅን ሳይበድል፥ ኪናዊ ውበትን ሳያሻሽር ጎልተው እንዲታዩ ማድረጉ፥ ከአንድ ዘመን እውነት ውስጥ ዘለአለማዊ እውነትን ማርቀቁ ነው።...... የለመድነውን ልበለዳዊ የትረካ ስልት በማርቀቅና ወደ ወሳሰበ ተምሣሌታዊ ትረካ በማሳደግ ታሪክን ከዛሬ እውነታችን አንጻር መልሶ የተረጎመበት «ከአክሱም ጫፍ አቁማዳ» በዓለም ስነ ጽሑፍ ታሪክ እጅግ ገናና ዝና ካላቸው ጥቂት ኤፒካዊ ግጥሞች የሚስተካከል ነው....... «ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ» ግጥም አማርኛ የተዋወቀው አንድ ንፅስ ግን ከፍ ያለ ጥበባዊ ፋይዳ ያለው የአጻጻፍ ቅርፅ፥ ‹ጦማር ግጥሙ ልንለው ስንችል፤ በተናጋሪው ህሊናና ልቡና ሲፈላ የምናደምጠው ሃሳብ፥ ለአንድ የተወሰነ፥ ነገር ግን በግንባር ለምናየው ተደራሽ፥ በደብዳቤ የሚላክበት መልዕክት ነው።...... የእምነት መናድ፥ የእውነት መሰወር፥ የህልም መበተን፥ በእውነታ መባነን ነው፤ ‹ጨፌ ላይ ተኝተው ባድማ ላይ ነቁ› እንዲል ራሱ ደበበ በሌላ ግጥሙ፤.......በእኔ አስተያየትና ግምት ይህ የራስ - ለራስ ባይተዋርነት ለአማርኛ ስነ ግጥም አዲስ ጭብጣዊ ጉዳይ ነው።» (2001 መድበለ ጉባኤ ገፅ 190 -191)

ደበበ ነፃ ግጥምና ዝርግ ግጥም - prose poem - የመጻፍ አቅም ቢኖረውም በአመዛኙ ያደላው ለነባር አጻጻፍ ቅርፅ ነበር፤ ነባር ይሁን እንጂ እሳቦቱ በዘመነኛ ህይወት ዋልታ ዙርያ ነው ያጠነጠነው። ደበበ በየካቲት መጽሔት (ታኅሣሥ 1974) ስለ ኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እድገትና አቅጣጫ በቃለ መጠይቅ እንደተናገረው «በደምሳሳው አንዳንድ ነገሮችን ለመጥቀስ የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ እንደ ገድል፥ ተአምር፥ መልአክ፣ ሰላምታ ያሉ ያጻጻፍ መንገዶች አሉት። እኒህን ምን ያህል የዘመናችን ደራሲ ለይቶ ተረድቷቸዋል? መጥቀም አለመጥቀማቸውን ፈትኗል? የግዕዝ ሥነ ግጥምም በጥቂት ስንኞች ሰፋፊ ሃሳቦችን መግለጽ እሚችል የራሱ የአሰኛኘት ፈሊትና የዘይቤዎች አሳሳል ባህሪይ አለው። ይህን ስይና በብዙ ስንኝኖች ጥቂት ሀሳቦች ብቻ ማስተላለፍ ልማዱ የሆነውና ዝርውነት ባያሌው የተጫነው ያማርኛ ሥነ ግጥም መለስ ብሎ የግዕዝን ሥነ ግጥም ባለ ማጥናቱ እጅጉን እንደተጐዳ እንገነዘባለን» ብሎ ነበር። ዕድሜ ተነፈገ እንጂ ያኔ ስለ ግዕዝ በጥናት የደረሰበትን በተግባር ያውል ነበር። ደበበ ግጥም ዕምቅ «ትርጉም አዘል ሰብአዊ ገጠመኝን ክረትና ኃይል፥ ፍላታና ቅርበት» መግለፅ የሚችለው በዘይቤና በጠበቀ ምት መሆኑን ያምናል። ለዚህም ነው ገና እድሜው ሃያ አራት (1996) በነበረ ወቅት ስለ እርጅና ረቂቅ እምቅ ግጥም የተቀኘው።

ዘመዴን ስስመው

ጉንጬ ቢሻክረው

እኔንም ሻከረኝ፣

ዕድሜ መለስለሱ፣ ማብቃቱ ታወቀኝ።

የልቦለድ ኖቤል ተሸላሚው Faulkner ጠቅላላ ችግራችንን ማሸነፍ ብንችል፥ ጊዜ ብቸኛ ችግራችን ሆኖ ይቀራል ብሎ ነበር። ደበበ በ«ጊዜ በረርክ» ግጥሙ ይህን እሳቦት ረቆበታል። ግን ወጣት እያለ «ዘመዴን ስስመው»ን ሲቀኝ እርጅና አሳስቦት አይመስልም። የግጥሙ ዕምቅነት የአንድምታ ጨረሮች መሸሸጉ ነው። ብዙዎቹ እንዳነበቡት እርጅና የሰውን

ውበት መፋቂ፥ በተለይ እንስት ከሆነች ሰቆቃዋ፥ የጊዘ ጭካኔ እንግልቱ ደመቀላቸው። በጥሞና ከተነበበ ግን የጊዜውን ፈውስ፥ ጠቃሚነት በየዋህነትና በብስለት መካከል የጎላቄ እርሾ መሆኑን ተቀኘለት። ግለሰብ የዋህ ጥሬ በነበረ ጊዜ ሌላው - ለዘመድ ቢሆንም - መረማመጃና መጠቀሚያ ነው። ዛሬ በሰለና ሻከረባቸው፤ ጊዜ አነቃው፤ አይነ ጥላው ተገፈፈ፤ የየዋህነት ዕድሜ አከተመ። ባለ ቅኔው በ«ወለምታ» ግጥሙ እንዳስተዋለው «ደቂቃ ዓመታትን ድል ስትመታ/ ገጠመኝ ገጠመኞችን ሲረታ» መሻከርም መብሰልም ነው። የሚያበቃ ረጅም ጐዳና ይሆናሉ። የአይን ግጥም ነው፤ ግጥሙ ትርጉሙን ምስሉን እንዲያመጣ ነው የተቀረፀው። ለዚህም ነው «የወህኒ አልጀብራ» የተባለው። ከታተመለትም ውስጥ «ቋጥኙ ተጠቃሽ ነው። ንጉሡ ስልጣናቸውን የተነጠቁ ዕለት፥ ቋጥኙ ድንገት ሳይሆን በትንንሽ እንቅስቃሴ ነፋስ፥ ሣር፥ ቅጠል፥ ድንጋይ......ሲያዋክቡት ተነጠቀ። የደበበ ልዩ ችሎታ የዘገባ ቃላት እንደ አብዮት፣ ትግል፥ ህዝባዊ ድል.....ሳይጠቀም፥ ሳይንዛዛ በምስልና በተምሳሌት የተከፈለውን ሂደትና ትዕግሥት ሳያደበዝዝ ተቀኘበት። ለዚህም ነው ያለፈ ታሪካዊ ክስተት ሳይኮማተር ለአያሌ ሁነቶች ወካይ የሆነው። ሥርዐት በትግል ሲናድ ማንበብ፥ ማድመጥ ብቻ ሳይሆን እናየዋለን። «ግና አንዲት ጠብታ፥ አንዲት ጠብታ /ውሃ ተሰኝታ/ አፈር ስትነክስ/ ድንጋይ ስትጐርስ/ ውቅያኖስ መርከብ እምታፈርስ / እና መች ቀረለት መነጠቁ/ ከግሽር ዳሱ መውለቁ»

እንዲያ እንዳልተንከተከተ

እንዳልሣቀ፤

ወረደ

ቋጥኙ

እየ

ተን

ሰቀ

ሰ

ቀ።

እንደ ዘመናችን መንፈስ ቋጥኝ የተለየ ትርጓሜ ይሰበስባል።

ደበበ ለመጽሐፉ መጠሪያ የመረጠው የብርሃን ፍቅር የአንድ ነጠላ ግጥም ርዕስ አይደለምና ስብስቡን ይወክልለታል። በደልና ቀርነት ጨለማ ናቸው፤ ድልና ነፃነት ብርሃን ይሆኑለታል። «ጥቁር አፈር አቅፎን/ ጥቁር ብርሃን ውጦን» በማለት እሳቦቱን ያሰፈዋል።

ከበባው ሲበዛ

ብዝበዛው ሲንዛዛ

ከጨለማ ጥጋት በውስጤ የበቀለች ያቺን ዘሃ ብርሃን አራግቤያታለሁ

ዙሪያዬን ጨለማ ቀጥቼበታለሁ

የፋኖ ፋናዬም ሁና አይቻታለሁ።

.................

እነሆ በቃነ

በዐይናችን ለማየት ደምቃና ተፍካከታ

ቷ ብላ ፈንድታ።

(«መስከረም»)

የጨለማን ገበና በብርሃን ነው የተረተረው። የባለቅኔ ምጥ ብርሃንን መገላገል መሆኑን ያተርኩርበታል፤ «አይደለም» በሚለው ግጥሙ ለኪነጥበብ ማደሩ ምርጫው ስቃይም ደስታም እያከለ ብርሃንን ለመገላገል ሲል የዘልማድ ጉዞ አልመረጠም። ተጨማሪ ብርሃን፥ ወንድና ሴት በፍቅር

ሲቀልጡ የሚፈካው ቦግታም ነው። ደበበ ለፍልስፍና ለዕውቀት ተቀኝቷል። ለልጅነት ትዝታው፥ ለቦረቀበት መንደርና ባህል በግጥሞቹ ተመስጧል። የሀገር የጭቁን ወገን ዕጣ ፈንታ በሰው እንጂ በሆነ መለኮታዊ ሃይል እንደ ማይቀና እንደ ማይጐብጥ ተገንዝቧል።

ደበበ ጥቂት የማይባሉ ጥልቅና ውብ ግጥሞች በፍቅር፥ በተባዕትና እንስት መተሻሸት ዙሪያ ያጠነጥናሉ። ከልጅነት እስከ አዋቂነት እየቀመሩ ገጠመኞች ተጠላልፈዋል። በ«እቴቴ» ግጥም ተራኪው ልጅ እያለ፥ ከወንዝ ለማጠብና ለመታጠብ ያጀባት ቆንጆ ወጣት፥ ከአደገ በኋላ፥ የወሲብ ጣዕም ከገባው በኋላ ትዝ ስትለው፥ ጊዜ ከጊዜ ይላተማል። ተናጋሪው አድጓል፣ እሷ ግን እድሜ ባከናነባት አስቀያሚነት ሳይሆን ገና ከወንዝ ስትንቦጫረቅ በነእብር ውበት ነው ድቅን የምትልበት። «ታዲያን ዛሬ በጉርምስና ዘመኔ/ ያ የጥንቱ ትይታ ተመልሶ መጣ ካይኔ/ ውስጥ ስትንቦጫረቅ/ ጸጉሯን ወደ ኋላዋ እየሳበች እየጐተተች/ ጡቷን ለፀሐይ እየሰጠች እየለጠጠች/ ኋላዋንም ነካ ነካ - ነካ እያደረገች፤» በልጅነት አዕምሮ ውስጥ ያንቀላፋ ትዕይንት ሲያድጉ ምስሉ ሳይደበዝዝ ለፍትወታዊ ጣዕም አቃሰተ። ሴቷን ዕድሜ አልፋቃትም።

በ«ተይው እንተወው » ፍቅር ዳር መውጣት ከተሳነው፥ ለትውስታ አስረክበው በሌላ የሕይወት ውጣ ውረድ እንድንጠመድ ያነቃቃናል። ደበበ የተቀኘላቸው ፍቅር ከለገሳቸው አገልግል አንድ እፍኝ ብቻ ዘግነው አገልግላቸውን የተቀሙ ጥንዶች ናቸው። ሆኖም የኑሮ ሰቀቀን ለፍቅር ብቻ በማደር መች ይረግባል? ሌላ የሚሰጡበትን፥ የሚያለዝቡት የሚተሻሹት..... አያሌ የጎላዌ ንጥረ - ነገር አድፍጠዋል። ለዚህም ነው «ተይው እንተወው» በነጠቁት ፍቅር ተወስነው፥ ጣዕሙን ለትዝታ አደራ ያስረከቡት። የኛ ማኅበረሰብ ለፍቅር ጉዳይ ያዙኝ ልቀቁኝ እያለ ህይወትን በሚያደፈርስ ታሪክ የተደመመ ነው። ደበበ ግን የሰከነ ልቡን ብቻ ሣይሆን አእምሮውንም የሚያደምጥ አፍሪቃ መልምሎ ነው በግጥም የተናደፈው።

በተለይም በአማርኛ ሥነ ግጥም ወደር የማይገኝለት ግላዊ ኑዛዜ Confessional poetry - የሚወክል በሁለት ገጾች የተፍታታው «ቅዠት.... ቅዠት» ግጥሙ በይበልጥ ተናዳፊ ነው። የሴትን ውበትና ገላ አፍቅሮ የአስተሳሰቧን ረግረግነት ጠልቶ፤ የእስትንፋስ ስቃይ ሲያጐሳቁለው ደበበ ያቃሰተበት ቅኔ ነው።

ልዩነት ይረዳዋል፤

መደዴነቷን ያውቀዋል።

ልቧን ገልጦ ያየ ሲመስለው

ቤሀ ነው እሚሣቀቀው።

ተስፋ እሚቆርጠው።

ይሁንና አፍቅሯታል፣

ተራነቷ ሳይተፋው፤ ‹ልዩ› ናት ሲል አምልኳታል።

.........................

ግን ሀክ ብሎ ላይተፋት፣

ነብሱ ውስጥ ተሸንቅራ

ተቀርቅራ።

የደበበ ግጥሞች ሳይቀዘቅዙ ዘመን ይሻገራሉ፤ እርግጥ በትግልና እንግልት ሀገርና ህዝብ ባቃሰተበት ዕለት የተቀኛቸው አንዳንድ ግጥሞች ዘመኑ ሲለወጥ እንደዚያን ወቅት እያማልሉን ይሆናል - ጥቂት ናቸው። በአድም ግጥም ሳይንዛዛ፥ ስለሚቀኘው ጉዳይ በመመሰጡ፥ የተንጋጋ የሚጋፉ ስንኞች አይገራም። ውብ ልዩ ግጥሞች አሉት፣ እየተረከ፣ እንደ ተውኔትም እየተቀኘ የጻፋቸው። ባለ አንድ አንጓ አጭር ግጥሞቹ ተነበው ምናባችን ውስጥ የመፈንዳት ጥበባዊ አቅም ቋጥረዋል። ተረትን ታክኮ («በተረት ላስላስል»፥

«እና»፥ «አዶለሴ» ወዘተ.) የፃፋቸው፥ ለየት ያለ አቀራረቡ ለጭብጡ ለጋነት ለግሶታል። ደበበ አንድ አብይ ባለ ቅኔ ነው። የግጥሞቹን ውበትና ጭብጥ ለማጣጣም ሰፊ ሂሳዊ ጥናት ይሻሉ። የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ በተለይም ሥነ ግጥም ላይ የሰራቸው ጥልቅ ወረቀቶች በአንድ ስብስብ መታተም አለባቸው። ሙሉ እና በለ አንድ ገቢር ተውኔቶቹ ግጥሞቹን የማደናገዝ እሴት አላቸው፤ ለመድረክም ለንባብም ደበበ ረቆባቸዋል። መች ይሆን የሚታተሙት? ቢሆንም በዚህ መድበል የደበበ ግጥሞች ዳግም የህትመት ብርሃን ማየታቸው ለእኛና ለዘመኑ ብስራት ነው። ለሁሉም በድሉ ዋቅጅራ ለደበበ የተቀኘውን መዘመር ወደ «ብርሃን ፍቅር» ግጥሞች እንዝለቅ።

ደበበ፤

ሳርም የኖርኩት ማሳ፥

ያልጠመደ ቢያመርትበት፤

ለፀበል በማኩት ቦይ፤

የግፍ እንባ ቢወርድበት፤

አንተን በእኔ ውስጥ አየሁት፤

ዘመንን አኩርፎ፥

በራፉን ቆፎ፥

ካንዲት ቀሪ ወዳጁ፥ ከነፍሱ ተቃቅፎ።

=======//////======

# እንደ መነሻ

ይህ ቅጽ እስካሁን ድምር የሥነ ግጥም ሙከራዎቼን ሲሶ ያህል የያዘ ነው። ከእነዚህ ሲሶ ያህሉ ደግሞ ገሚሶቹ በቅድሙ አብዮት የተጻፉ ናቸው። ቅድመ - አብዮት የልጅነት ግጥሞቼ ለድኅረ - አብዮት የጐልማሳ ግጥሞቼ፣ ባያሌው አበው እንደ መሆናቸው ዐሥራዉ፣ በጅምላ ልገድፋቸው አልፈለኩም፣ በድምሩ ልዘላቸው። ስለዚህም ነው ኅትመት ፋና ወጊ ሁኗቸው ወደ እናንተ ውድ አንባቢዎቼ ስሸኛቸው፣ ብኩርናቸውን እንደ ጠበቁ እምታገኟቸው።

ስለ እኔው ግጥሞቼ እኔው ማሔስ የለብኝም። እሚገባም አይመስለኝም። ይህማ፣ ሌላው ቢቀር የብርቱ አንባቢዎቼን አስተውሎት መጠየቅ ይሆንብኛል፤ በእሽቅድድም መንጠቅ። በሌላ ረገድ፣ ከሒስ መደብ እማይገቡ ጥቂት ነጥቦችን ብወራውር መልካም ይመስለኛል - በተለይም በድግምግሞሽ በግጥሞቼ ውስጥ ስላነሳኋቸው ርእስ ነገሮች።

የዕድሜዬን ግማሽ ለሚያህል ጊዜ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተማሪነና በመምህርነት እንደመቆየቴ፣ የምሁራንን ጉዳይ የግጥሞቼ ጉዳይ ያደረኩበት ጊዜ ጥቂት አይደለም። ለምሳሌም ቅድመ - አብዮት ግጥሞቼ መኻል፤ «ድንቁም መምህር» ፤ «ጥሬ ጨው»፤ «ሰማይና ምድር»፤ «እማማ.....እማማዬ፣ » እና «ያባትህ ልጅ» የተሰኘው በቀጥታ ምሁር ነክ ጉዳዮችን እሚያወሱ ሆነው የወቅቱን የተማረ ትውልድ ሀገርተኛነትና ሕዝባነት እሚጠይቁ ናቸው። በፊውዶ ቡርዧ መስፈራርቾ ሥርዓት መወግሸቱንና የማንነት መለዮውን መጣሉን እሚያንጐራጉሩ። ይህ ይሁን አንድነታቸው እንጂ ጉልህ ልዩነትም በመኻላቸው አለ። «እማማ እማምዬ፤» ሀገርኛ መለዮውን አጥቶ የነበር አጥቶ የነእብር ትውልድ የፀፀት እንጉርጉሮ ነው። በሌላ ገጹም የራስ ግንዛቤ የተሐድሶ መዝሙር። «ያባትህ ልጅ» ግን፤ «አንቺ ልጅ ኩሪባቸው በእንግሊዝ አናግሪያቸው» የተሰኙትን ስንኞች የዘፈነው (ያዘፈነውን)

ትውልድ ረግረጋማነት ባንድ ፊት፤ በሰማየ ሰማያት «ቋንቋ» ካልሆነ በባላገር ልሣን አንደበታችን አይጨቀይም (ምድራዊ አይሆንም) ይሉ የነበሩትን አንዳንድ የቀደም ሊቃውንት መሠሪነትን በሌላ ፊት፤ - በማንጸር የተወረወረ የታዛቢ ቁጣ ነው፤ በትር። በተረፈ በሁለቱም የሀገርተኝነትና የሕዝባዊነት ድምጾች ቢሰሙም፣ በመጀመሪያው ሀገርተኝነት ነው ይበልጥ እሚጎላው። በሁለተኛው ደግሞ ሕዝባዊነት።

ይኸው ጉዳይ በድኅረ - አብዮት ግጥሞቼም ውስጥ መዛመቱና እንደገና መከሰቱ አልቀረም። ምሳሌ ቢያስፈልግ «ሐዘንሽ አመመኝ» ንና «ለድንገት - በቀል ፈላስማ ዐርበኞች» የተሰኙትን መጥቀስ ይቻላል።

«ሐዘንሽ አመመኝ፣» እንደ «እማማ.....እማምዬ» ሁሉ ከተማረው ትውልድ መኻል በሥጋም በመንፈስም ከሀገሩ ርቆ የነበር ወገን እሚያሰማው የቅሬታ እንጉርጉሮ ነው። የብክነት ዐይነጥላው ተገፎለት ራሱንና ሀገሩን ማተኮር ሲጀምር ከውስጡ እሚብሰከሰክ የነፍሱ ጩኸት ነው - የናፍቆት፤ የፀፀት እሮሮው። በሌላ በኩል ግን፣ እሱና በየሱነቱ (ማለት በሀገሩ) መኻል የቆመውን ማገኛውንም ገደል አፈራርሶ እሱነቱን (የእሱነቱን መለዮውን) የመፈለግና የማግኘት ቁርጠኝነቱ እሚሰማበት የብሩህ ተስፋው መዝሙርም ነው።

እርግጥ ነው፤ «ሐዘንሽ አመመኝ፤» እጅግ አያሌ ኢትዮጵያውያን በረኃብ በሚረግፉበት ወቅት የተፃፈ እንደመሆኑ ከሌላኛው ግጥም ይበልጥ ስሜትን ሊጫን ይችላል። ሊያም። ሁኖም ብሥራት ፍጹም የተለየው አይደለም ውጋጋን። ቀቢፀ - ተስፋ ያደቀቀው ትውልድ ድምፅም አይደለም፤ ከቶም።

ሁለቱም ግጥሞች የተማረው ትቅልድ ዐይን ላይ ወድቆ የነበረውን መንታ ጭምብል ያሳያሉ። ማሳየት ብቻም ሳይሆን ጭምብሉ በተራው ሲወድቅ፣ ትውልዱ ወደ እውነታው እውነት ለመቅረብ መብቃቱንም ያበሥራሉ። በ«እማማ.....እማምዬ» ሀገሩን ባዶ ማጀት አድርጎ ይገምት የነበረው ትውልድ፥ ቆይቶ መልካም ገጽታዋን ያያል። በ«ሐዘንሽ አመመኝ» ሀገሩ ሁሉ በጅዋ ሁሉ

በደጅዋ ትመስለው የነበው ትውልድ፣ የሚያስበውን ያህል እንደ ሌላት ያስተውላል። ዋናው ቁም ነገር፣ ሁለቱም ከጽንፋዊ አተያዮች ተነሥተው እሚደርሱበት ግብ አንድ መሆኑ ነው። ከራስ ጋር - ከሀገር ጋር ዕርቅ። ይህም የግጥሞቹ እንጉርጉሮነት ሳይሆን መዝሙርነት ይበልጥ ጐቶ እንዲሰማ አድርጓል።

በሌላ ረገድ «ያባት ልጅ» እና «ድንገት - በቀል ፈላስማ ዐርበኞች» እሚመሳሰሉበት ነጥብ አለ፤ እሚናጸሩበትም። ሁለቱም ከተማረው ዘመናዊ ትውልድ መኻል አንዳንዱን እሚያስታዝቡ ናቸው፤ ሕዝባዊነቱን እሚጠይቁ። ይህም ሁኖ፣ «ያባት ልጅ» ዕውቀቱን በአንደበቱ - አፍርንጅ ከብዙኃን እንዳይደርስ ያደረገውን ምሁር በስላቅ የሚሸነቁጥ ሲሆን፤ «ድንገት - በቀል ፈላስማ ዐርበኞች» ደግሞ፣ በተለይ ከ1966 መጋቢት እስከ ሰኔ በነበረው ጊዜ ከሥልጣን ርካብ ተንጠላጥሎ ከብዙኃኑ ሕዝብ ላይ ሊፈናጠጥ ከጅሎ የነበረውን አንደበተ ነቀልቃል ምሁር ይሞግት ሲባል የተጻፈ ነው፤ ያጋልጥ። ህሊናውን ይውቀስ ሲባል የተወረወረ ነው፤ ይቆንጥጥ።

በተረፈ (እሚዳበሉበት ወቅት መኖሩን ሳንዘነጋ) - ቅድመ - አብዮት ግጥሞቼ በጣሙን በግለሰባዊ ገጠመኞች ላይ የተመሠረቱ ሲሆን፣ በዛ ያሉ ድኅረ - አብዮት ግጥሞቼ ግን በሀገራዊ ገጠመኞች መነሻና ምክንያት የተጻፉ ናቸው። ከሁለቱም በኩል ካሉት መኻል በመገናኛ - ብዙኃን የተሰሙ አሉ። በመጽሐፍ ጥራዝ መገኘታቸው ደግሞ በቅርብና በድግምግሞሽ ለማጤን ያስችላል።

በያንዳንዱ ግጥም ግርጌ የተጻፈበት ዓመተ ምሕረት ሠፍሯል። በግጥሙና በተጻፈበት ወቅት አንዳች ጥብቅ ዝምድና ሲኖርም ወራት ታክለዋል። አንዳንድ መግለጫዎችም እንዲሁ።

ደበበ ሠይፉ

መስከረም - ፲፱፻፸፱

# ሙዚቃ - የምች መድኃኒት

ያለፈው ይመጣል
የሞተው ይነሣል።
እስቲ እህህ በሉ
በሉ እስቲ አንጐራጉሩ
የዘመድ የወዳጅ ይፈንቀል መቃብሩ
ይሰበር ሳጥኑ
ይገለጥ ከፈኑ
የምጽዓት እምቢልታ ዋሽንት ነጋሪቱ
ይስማው ልባችሁን ቀርነ መለከቱ።
ዐይን ዐይቶት ያለፈው
ልብ የመዘገበው
ሠራዊቱ ይንጋጋ የቅርብም የሩቅ
በሙዚቃ ሥዕል ይነደፍ ይድመቅ።
«ዋ! አለ አሞራ፥
ዋ......አለ
እጅዋን ሊበላ
ዋ......አለ
ዐይኑና ሊበላ

ዋ.........አለ

ዋ.........አለ አሞራ

ዋ........አለ።»

ትካዜ ለቅሶዬ

ልቤ መባባቱ

ላንጐራጉር ብዬ

ዐይኔ መሟሟቱ።

ስትሠርፅ ሙዚአ ትንሣኤን ደውላ

ከምድር ከሰማይ፤

ሙታን እንዲነሡ ያልታየው እንዲታይ

ብትጣቀስ ከእንባ ብታመጣም ብካይ

የዳዊት በገና ጉንጨን ብታቀላ

ሳኦላዊ ነብሴን ቁስሌን አድን ብላ

ሽከሜን አቀል ብላ።

በዘመናት አረም ተውጦ የቀረውን

በዝንጋዔ ደለ የተዳፈነውን

ዛሬ የመከሠቱ የሷ ቢሆን ጥፋቱ

መቼ ይርቃትና ከቶ አብነቱ?

ስንቶቹን አየሁኝ አንች የነብስ ነብስ

ሕይወትን ሲቀምሱ በአንቺው ምላስ

ጉሀና ቃና ሁሉ አንችጋ ሲደርስ
ጣዕመ መልካም ነው ምግብ መንፈስ።
    ይሁንም አንችዬ!
    ብርታቴ ይከዳኛል
ለአንቺው መሥጋቴን መደበቅ ምን ያሻል?
ከቶ እንዳትተይኝ መዐቴ ከብዶሽ
    ያለብኝን ጭንቁን
    ምሬቱን ሐዘኑን
        እንዴት ላዋይሽ?
        ይህም ሁሉ ሁኖ፤
    እየተጠራጠርኩ ማመኔም አልቀረ
    ታዳጊዬ እንደ ሆንሽ ከኔ አልተሠወረ።
በይ እንግዲህ በርቺ
    የትላንቴን እንቺ
        የጭንቅ ግማሽ፤
በይ እንግዲህ በርቺ
    የዛሬዩም ላንቺ
        የእንባዬ ስላሽ።
እንዲህ ካልተራዱ ካንቺ ብጤዎቹ
አጣድሮ ይገድላል የሕይወት ፀሐይ ምቹ።

# ተስፋ - ጨረቃ

አታውቅና መቼም
ሁልጊዜ መሸለም
ሁልጊዜም መሾም፤
ሕይወት አዱኛዋን
የውስት ዕቃዋን
ፍሥሐ ማዕረጓን፤
መልሳ ወሰደች።
ሳይቀር ወዳጆቹን
ከጎኑ አራቀች።
እሱም መደነቁ
በመልኳ አበዛዙ
ካብዋ መሞቁ
ውርጯ መቀዝቀዙ።
ተመኝ ቢጨንቀ
የሚያዘንበው እንባ፤
ጐርፍ ሁኖ ቢያደርሰ
ካለመኖር አምባ።
ዘመድ መኻል ሁኖ

የሚያዋየው አጥቶ
ወዳጅ መኻል ሁኖ
የሚጠራው ጠፍቶ
የነበረው ደርቆ
በአለው ግን ሲዋኝ
ጮኸ ራሱን አንቆ፤
‹ምንም አልቀረኝ
ሞቴን ለግሰኝ!›
ታዲያ ካፉ አይዘልቅም
    ይህ ተስፋ መቁረጡ
አለ ሌላ ዓለም
    ዘልቆ ሲታይ ውስጡ።
እሰው ፊት ነው የወቃው
    የእንባዉን አዝመራ፤
እሰው ፊት ነው ያእልው፤
    ‹ተስፋ ቢስ ነኝ
            ዕድለ ሰባራ!›
ግን በስውር ጣቶችህ ብትደባብሰው
በሕሊና ኤክስሬይ ብትመረምረው፣
ከዛ ብረትማ ውርጭ የልቡ ስናቃ

ተስፋን ታገኛለህ የሙጥኝ ተጣብቃ!
እንዲያ የጨለመውን
 የጽልመት የሆድ ዕቃ፣
የምታበራዋን
 ትጓጓን ጨረቃ።

# ድንቄም መምህር

ራሱን ሲከሽን
ሲያንቆለጳጵሰው
ማር - ወተት ሲያረገው
ከንፈሩን ሲስመው
 ሊያስተምረኝ መጥቶ፤
 ብሽቅ አደረገኝ
የተረብ ጋዘና መሆኑ ሰቀቀኝ።
ለጋ ጊዜዬ ላይ መሸናቱ ነደደኝ።
እንዳይሰማው ፈርቶ
ልቤ አንሾካሾከ፤
 «አስተምረኝ ባለ

ስንት ነገር አለ!»

## ብቸኝነት

ከተማው ተይዞ ሲታል ምድረ በዳ
ሰው ከራሱ በቀር ለሌላው እንግዳ
ሁኖ ሲውል ሲያድር በብቸኝነቱ
‹ሞተች!› ይላል ዓለም
ውስጣዊ ፍጥረቱ።

## ወፊቱ

የጎዋውን መንገድ እንዳንሸሽ ስታዝ
ሳትገጪ፤ ሳትገጭ በግብር ሳትያዝ
ተራራ ጫፍ ሁነሽ ተራራ ስታይ
አድማስ ሳይወስንሽ የትም እይት ስትይዝ፤
ኧረ ምን መሰለሽ?
ወደ ኋላ ያዘሽ?

መሸት ከማለቱ ያደነቃቀፈሽ?
ወፊቱ በሌሊት ምን ይሆን ታስቢ
እኔኑ መሰልሽኝ ጐጆሽ ስተገቢ።

# የሕይወት እጅ

ሚዳቋ የሚያባርር ነበር ሁኜ
ጨረቃን የሚያሳድድ ሕፃን ሁኜ
ልብረር ስል
ልብነን፤ ከጥላዬ ፈጥኜ፤
መሰለኝ።
ያንተ አይደለችም አለኝ።
ሣግ ሲተናነቀኝ
እየኮረኮረኝ።
ሲያስገለፍጠኝ
እየቆነጠጠኝ።

# ይረጋ ዓለም

ይርጋ ዓለም

ዋ......ይርጋ - ለም

የልጅነቴ ሕልም ቀለም

ዐይኔን የከፈትሽው ጨረር

ወርቅማይቱ ጀንበር

ዕፅዋት፥ ሥራሥር፥ ፍራፍሬ

ዶቅማ፥ ጐደሬ፣ እንጆሬ፤.....

የቅጠል እንግዳ የኩልቤት፥

እንሰት ቡና፥ ቡና እንሰት

ሲያለብስሽ ሲያከናንብሽ

ሲሞሽርሽ ሲያደምቅሽ

ላያከርብሽ፤

ካባውን ሲያጠልቅልሽ

ላይሾምሽ፤

ዛሬ ባስትውል ታዘብኩሽ።

የተፈጥሮ እምቢልታ ጥሩንባ

አረንጓዴ ቢጮህ ባንች አምባ

ማንስ ነቅቶ፥ እህ ሊልሽ?

ማንስ በቅቶ፥ ሊታደግሽ?
ናፍቀሽኝ እንደ ገሠገሥኩ
ጭቃ......ኮረት
ፍራሽ.......ዝገት
    ሁነትሽ ስጋኝ
    ምን ይዋጠኝ?
አባ ወራው እንደ ሞተበት
ወራሽ እንዳለማበት
    ገፊ ቤት፥
ሲያይ ስትዘነጣጠይ
እሚጠግንሽ ጠፋ ወይ?
ሰዎችሽ ሸሹን፥ ሔዱን?
ወደ ደራበት አመራሩን?
እንደ አሮጌ ጨርቅ ሲጥሉሽ
ማን ይጠቃቅምሽ አሉሽ?
በቅሬታ ታዘብኩሽ።
አንቺ ብቻ የማትቀልጪ
በላብ በወዝ የማትበልጪ፥
    ለምን?
ድጅኖ መዶሻ አካፋ

ጠረኑስ ካንቺ የጠፋ፥

ለምን?

ባጥቢያሽ የገደል ማሚቶ መተኛቷ

በቦዘን ምክንያት መደፋቷ፥

ለምን?....እኮ ለምን?

ምፅዓትሽ አይቆጠር

አልሞትሽም እሚሉ ለገር።

አለሽ እያሉ ሲቀብሩሽ

በቅሬታ ታዘብኩሽ።

ግዴለሽም፥ ብሶትሽን አትደብቂ

ጉልበትሽን አበራቺ፥ አነቃቂ

ፍቅርን በወዝ ሰንቂ።

እንዳሽለብሽ እንዳትቀሪ

ነቃ ማለቱን ድፈሪ።

ዕፅዋቱን ተመርኩዘሽ

ተንሺ.....እባክሽ ተነሽ፤.....

ይርጋ ዓለም

ዋ......ይርጋለም

የልጅነቴ ሕልም ቀለም

ዐይኔን የከፈትሽው ጩረር

ወርቅማይቱ ጀምበር።

# ሰማይና ምድር

በጀርባዬ ተንጋልዬ
 አውዬ
አፍላጦንን ከራስጌዬ፤
ሔደ ሰማዩን ቀዶ ሕሊናዬ።
በቅጽበት የፈተልኩትን ለብሼ
 ሞቆኝ፤
በኔው ዓለም እኔው ነግሼ
 ደልቆኝ፤
ከጽድቁ ገበታ ቀምሼ
 ጣፍጦኝ፤
ቀና ብል፤
ያቻት ጐጆዬ ደብዝዛ
እንደ ከፉ ቀን ቀዝቅዛ፤
ንፋግ ፍቅሯን ለማየቱ
ብርሃን እንኳን መታጣቱ።

# ያቺ ቆንጂት

ያቺ ቆንጂት ትመጣለች
    እያዜመች
እማማዋ ሲወጡ
ቡና ሊጠጡ።
«ጋሼ ላጫውትህ?» ትለኛለች
ያይኔን ብርሃን እየሞቀች
«እሺ ቆንጂትዬ» እላታለሁ
መጻሕፍቴን እየገፋሁ።
ትጫወታለች
የባጥ የቆጡን ታወራለች
ቆንጂትዬ፤ ዐይናምዋ ቆንጂትዬ
ጥርሷን ፍልቅቅ እያደረገች
ከንፈሯን እያፋተገች
    ትንከተከታለች፤
(ግን ድንገት ልታቋርጠው
ስሜቷን አንዳች እንደሚገስፀው)
«ምነው ቆንጂትዬ?»
«ምንም አይደለም ጋሸዬ»

ብር ብላ ትሔዳለች
ብር ብላ ትመጣለች
ፈደሏን በጅዋ ጨብጣ፤
(ዐይነ ጥላ ነበረባት
ትምህርት እሚከለክል)
«አታስተምረኝም?» ትለኛለች
ያይኔን ብርሃን እየሞቀች
«እሺ ቆንጂትዬ» እላታለሁ
መጻሕፍቴን እየገፋሁ።
አጠገቤ ትቆማለች
ቆንጂትዬ
ስንጥሯን እንደ ጠቆመች
ጣቴን ያዝ እንጂ እያለች።
ይዛትና
ሀ - በይ ስላት
ሁ - በይ ስላት
እንቆይና
የጣቷ ላብ ሲያዳልጠኝ
‹በ›ን ጠንቁላ ‹ቀ› ስትለኝ
አያትና

ድምፃ ሲደክም እሰማና፤
«ምነው ቆንጅትዬ?»
«ምንም አይደል ጋሽዬ»
ብር ብላ ትሔዳለች
    ቆንጂትዬ
    እንደገና ልትመጣ፤
    (አፍታ ሳትቆይ)
    «እንደ እማዬ አታለብሰኝም?» ትለኛለች
    ያይኔን ብርሃን እየሞቀች
    ‹ነይ ላልብስሽ› እላታለሁ
    መጻሕፍቴን እየገፋሁ።
    አለብሳት ስል አይሰማማት
    አንዴ ሲያጥር ሲረዝምባት
    ግራ ገባኝ
    ግራ ገባት።
    ፈርዶባት።
    ፈርዶብኝ
    ፈርዶባት።
ብር ብላ ሔደች ቆንጂት
በማግሥቱ እኅቴ ናት

ነጠላዋን የሰጠቻት።

# እማማ....እማምዬ

እማማ እማምዬ.......

የኔነት መደብ ሙብቀያዬ

የኔነት ቀለም አሻራዬ፤

እስቲ፥ እንምከር እንወያይ

ገበናሽ ገበናዬ

ተፈልቅቆ እየታዬ።

ከማሕፀንሽ አምባ ባቅዬ

መልክ ስምሽን ከመልክ ከስሜ አንጠልጥዬ

ግርማ ሞገስሽን ተካፍዬ

ያለውለታዬ፤

ሰሐሽን ተቀብዬ

ያለ ዕዳዬ፤

ዕድልሽ ከዕድሌ ተቆራኝቶ

ገነቴ በገነትሽ ተመሥርቶ

ፍዳዬም ከፍዳሽ ተጋርቶ፤

ምነው ታድያን ቆይቶ ይታየኝ ጀመር ተለያይቶ

ያዋደደን ገመድ ተፈቶ

ውጥሩ ረግቦና ላልቶ?

ምንድን ሆነ እማማዬ፥ በመኻላችን ምን ነፈሰ?

ቃልሽን ከቃሌ ያበሰ፥ ውላችንን ያፋለሰ

ገጽሽን ከዐይኔ የገሠሠ

ምድን ሆነ እማዬ ሆይ፥ በመኻላችን ምን ነፈሰ?

ብትጠሪኝ እንዳልመልስሽ

ብትልኪኝ እንዳልላክሽ

ፊቴን አዙሬ እንዳልፍሽ

ብትቀርቢኝ እንድርቅሽ

ብታወሪ እንዳላዳምጥሽ

ብትጽፊ እንዳላነብሽ

ውሸት ብዬ እንድሥቅብሽ

ተረት ብዬ እንዳገጥብሽ

ያደረገ፥ ምንድን መዓት ተተኮሰ

ምንድን ሆነ እማማዬ፥ በመኻላችን ምን ነፈሰ?

ቃልሽን ከቃሌ ያበሰ፥ ውላሽንን ያፋለሰ

ገጽሽን ከዐይኔ የገሠሠ

ምንድን ሆነ እማዬ ሆይ፥ በመኻላችን ምን ነፈሰ?

እባክሽ፥ ዘራችን በውል ይታወቅ
በወግ ይቆጠር አይደበቅ
በመጤ ተረብ አይታመቅ
በባዕዳን ክርን አይድቀቅ፤
እኔና አንቺን እሚያውቀን
የታሪክ ልሣን ይፍረደን፥
ሲይዙኝ በጠይምነቴ
ፀሐይዋ አትሁን ምክንያቴ።
እማማዬ፥
ከዶቃው ጋር ከአፈሩ
ከዳዴው ጋር ከእሹሩሩ
ከሕመሙ ከጭንቀቱ
ከቡረቃው ከሐሴቱ
ከበጋው ከክረምቱ
ከብርዱ ጋር ከሙቀቱ
የነበርሽ - የተካፈልሽ፥
አሁን ወዴት ይሆን ያለሽ?
　　በይ፥ አምባሻ የለሽም ወይ ዳቦ
　　ጨጨብሳ የለሽም ወይ ጭኮ
　　ጐመን የለሽም ወይ ክትፎ

ቆይጮ የለሽም ወይ ገንፎ፤
ያንቺን ገበታ ደፍቼ
ጽዋሽን በእጆቼ አንከቼ
የባዕድ ማዕድ ስመጥን
ወጥሽ ሻግቶ ይደፋን? የደፋን?
ጠላሽ ሽምጥሮ ይፍሰስን? ይፍሰስን?
ብፈራ ነው በሰው ምላስ
ቃናሽ ኋላ እንዳይዳስ፣
ተራርቀን እንዳንቀረው
ተመዝነን እንዳናንሰው
ብፈራ ነው እማምዬ ብጨነቅ ነው።
የሕይወትሽ ማኅደር ብራና
እንደያዘ ያንቺን ዜና
ሳይገለጥ እቅን ያልፍና
ሳይነበብ ሳይወራ ይቀርና፤
እንዳይደድቡ ዐይኖቼ
ልብ ሕሊና ጆሮቼ
የሕያው ገጽሽ ውበቱ
እንዳይነጣ ደም ግባቱ
ዐመዱ እንዳይቀር ዐለቱ

ኮረቱ እንዳይቀር ሐውልቱ።

ብፈራ ነው እማምዬ፥ ብጨነቅ ነው

ተራርቀን እንዳንቀረው

ተመዝነ እንዳናንሰው።

ካንቺ ርቄ - ከኔ ርቄ

ከየምናምኑ ወድቄ

በሌላው ዕድር ጠልቄ

ልናገር ብል - ማን ሊሰማኝ?

ልጐብዝ ብል - ማን ሊያኮራኝ?

እባክሽን፥ አስተምሪኝ አልተማርኩም

ጥላቻሽን ሳለመልም፥ ፍቅርሽን ገና አላወኩም።

በአርያሽ መፈጠሬን

በፈለግሽ መወሰኔ

መወለዴን ባንቺ ልደት

መቦረቄን ባንች ልጅነት

መፈንደቀኤን ባንች ተረት፤

- እንደምሞትም ያንቺን ሞት -

አስተምሪኝ አልተማርኩም
ጥላቻሽን ሳለመልም፣ ፍቅርሽን ገና አላወኩም።

እማማ እማምዬ፣

የኔነት መደብ መብቀያዬ
የኔው ቀለም አሻራዬ፥
የነብሴን ልጣን፣ ካንቺው ጉያ - ካንቺው ገላ
ዳግም ከቶም አልሁንብሽ ተቀጥላ
የወግ ልጅ የይስሙላ።........
ቃል ኪዳኔን ተቀበይኝ
የኔ ሁኚ፥ ያንቺ አድርጊኝ
አልለይሽ፥ አትለይኝ -
አይበድሉም ብበድልሽ
መቼም የትም እናቴ ነሽ .........እናቴ ነሽ።

## ዳኢት (አንዲት የሲዳሞ ሴት)

መላ ሰውነቴ እያነባ
ነብሴ ሳትቀር ተንገብግባ
    በፀሐይ ፀሐይ
    ይርጋዓለም ከቀትር ላይ፤
ዝዬ እንዳልወድቅ
እርምጃዬን ሳጠብቅ፤

አቧራውን እየጫረች

በጣቶቿ

በጥፍሮቿ

ሸንኮራውን እየፈጀች

ልጣጩ ሳይቀር እየመጠጠች

እያገላበጠች፤

ትጓዛለች

ዳኢቴ.......ትሔዳለች

ፊት ለፊት ትነጉዳለች።.......

(ከገበያ መልስ

የኑሮ ምሱን ለማድረስ)

ሹርባዋ በቀጭኑ ተሠርቶ

የቅቤ ያለህ ከሚል አቧራ ተገናኝቶ

የቆዳ ግልድሟ እየተንኮሻኮሸ

ፍርጥም ያለው ጭኗን እያሻሸ

ትሔዳለች

ትነጉዳለች።......

ጥብቆዋ እንደ ሸሚዝ ያጠለቀቻት

እንዴት ነው የምታምርባት?

ደርደሮነቷ እየተንጨፈጨፈ

ገላዋን

አመስ አመስ የተደረገ

ቡናማ ቀለሟን

እያርከፈከፈ፤

ጨሌዋን ደሞ ዶቃዋን

ያስጌጠችበትን አንገቷን

እያበሳባት

ቅቤውን እየከለሰባት፤

እያየኋት......እያየኋት

ታሳዝነኛለች ዳኢቴ፤

ገና ብዙ.....ብዙ ብዙ ትጓዛለች

በፀሐይ ፀሐይ

ይርጋለም

ከቀትር ላይ

# አዴ ላንቃሞ (አንድ የሲዳሞ ወንድ)

ብርማይቱ ጨረቃ

የብርሃን ጠበል አፍልቃ

ተፈጥሮን ስታጠምቃት

እንደ ገና ስትወልዳት

ነፋሱ በቀስታ

በበረዶ እጁ ሲማታ፤

አዴ ላንቃሞ

ጦሩን ከጎኑ አጋድሞ

ያስተውላል እንደ ነገሩ

አሽቆቁሎ ከሥሩ

እንደ ዘበት

አፈርሣታ የቆመበቱን

የእንሰት።

ጥች ይጨሳል ዐልፎ ዐልፎ

ለአዴ ላንቃሞ

እየተዳፈነ ነው ቀቄሎ፤

በቅቤ የጠገበውን

ቡልኮውን

ገለጥ እንደ ማድረግ ብሎ

ሆዱን ሲያሻሸው

እድኒርበው

መልሶ ተወው

ብርድ ነከስ ቢያደርገው።

ከዛም ታየው.......ታየው ባእምሮው

እንደ ደግ ሕልም ደስ ደስ እያለው

ሦስቱም ሚስቶቹ ሲርመጠመጡ

የሱን ጉሮሮ ሊያጣፍጡ።

በልቡ አደመጠ ሲመታ

የያንዳንዷን ልብ ድርብ ድርብ

ሽቅብ ሽቅብ

በ«እኔጋ ነው የሚያድር ዛሬ ማታ»፤

አዴ ላንቃሞ

የዘወትር ጭምቱ

ቀልድ ቀልድ ሲለው ብልሃቱ

(ከዐልፎ ዐልፎ አንድ ዕለት

እየከፉ እንደ መዝናናት)

ወደ ጐጆአቸው ተጉዞ

ሚስቶቹን ይመጣል አዞ፥

«እራት እንዲበስልልም
አዳሬን እመጣለሁ፣፤»
ታዲያ እንዲህ እንደ ዛሬው
ብርማይቱ ቸረቃ
የብርሃን ጠበል አፍልቃ
ተፈጥሮን ስታጠምቃት
እንደ ገና ስትወልዳት
ነፋሱ በቀስታ
በበረዶ እጁ ሲማታ፤
ካፋፏ ላይ ቁጭ ብሎ
ጭሱ ሲወጣ ተጥመልምሎ
እያየ፥ ፈገግ ፈገግ ይላል
ከት ከት ብሎ ይሥቃል
ወንድ የመሆንን ጽድቅ የከባል
የደንቃል።
ደሞም ይፈልጋል
ማወቅ ማረጋገጥ
መገኖ እንደ ሰጠው
ምኔም እንዳይነፍገው
ለእያንዳንዷ ሰዓት

በያንዳንዷ ሌሊት

ሦስት ሴት ከሦስት ራት።

እግራቸውን ታጥበው

በቅቤ ተሻሽተው

በጢልቴ ቆጮውን

በጮጮ ወተቱን

 አሳምረው.....አምረው

ሲጠብቁት ሲያውቀው

ሦስቱንም አፍቅሮ

ግን አንዷጋ አድሮ

ባንድ ራት - ባንዲት ሴት

ተሰልባ ያች ሴት

ሌላው ሳያገኘው

ግን እንደ ተመኘው

ማደሩ ትዝ ሲለው

መብቱ እየተሰማው፤

እንዲህ እንደ ዛሬው

ብርማይቱ ጨረቃ

የብርሃን ጠበል አፍልቃ

ተፈጥሮን ስታጠምቃት

እንደ ገና ስትወልዳት
    ነፋሱ በቀስታ
    በበረዶ እጁ ሲማታ፤
ካፋፉ ላይ ቁጭ ብሎ
ጭሱ ሲወጣ ተጥመልምሎ
እያየ፥ ፈገግ ፈገግ ይላል
ከት ከት ብሎ ይሥቃል
ወንድ የመሆንን ጽድቅ ይከባል
            ያደንቃል።
እንዲህ እንደ ዛሬው ሞቅ ሲለው ልቡ
ይሣካለት ይሆን ያቀደው በቅርቡ?
አንዲት ጐጆ ነገር ጥቂት ቀን ሸፍሽፎ
አንዲት ጊደር ቢጤ ገዝቶ ወይም ዘርፎ
አራት ከአራት አርጐ መብቱን ማጐልበቱ
            ቀልዱን ማፋፋቱ?!

# እቴቴ

ድሮ ነው ፊት
በልጅነቴ ሰዓት፤
ፉራፉሬ ከማበርት ቦታ
    መጥታ
ትጠራኝ ነበር ያች እቴቴ
    የጐረቤቴ፤
«ቡና ናፍ ወንዝ እንውረድ
ሸንኮራ ቆርጨልህ እንድትጐምድ.....»
«እሺ እቴትዬ» ብዬ
ጣሳውን ከእጅዋ ተቀብዬ
እከተላታለሁ ወንዝ እቴቴን
    እቴቴ - የጐረቤቴን።
ውሃውን
ፀሐይዋ ስታፀኸየው
በወርቅ መርገፏ ስታጌጠው
እቴቴም
ጨርቋን ስታንጨፈጭፈው
ስታሽ ስትጠመዝዘው

ስትዘረጋ ስትቀለብሰው፤

ደሞም ስትዘፋፍነው

«የኔ ቤት እቆላ ያንተ ቤት አፋፉ

ልቤን አመጡልህ እየደጋገፉ»

ልትለው......ስትለው

ትንሹን ልቤን እንዴት ነበር ደስ የሚለው

ደስ የሚለው?

ታድያ አፍታም ሳትቆይ እቴቴ

እቴቴ የጐረቤቴ

ዘረረረር አድርጋ ልብሷን

ውሃ ውሃ እሚል ጨርቋን

ሣሩ ላይ ጉቶው ላይ

በየቅርንጫፉም ላይ፥

ትለኛልች እኔን

እኔን ትንሹ ቡጡን

ውሃው ውስጥ የምንቦራጨቀውን፤

«እስቲ ደሞ ተራዬን

እኔ ልታጠብ ገላዬን

አፋፏ ላይ ቁምልኝ

መንገድ መንገዱን እይልኝ

ሰው አለመምጣቱን ጠብቅልኝ......»
እሺ ብዬ ዲዲዲዲ ወዳፋፏ
እሷም ፈታ ፈታ መቀነቷን
ገልመጥ ገልመጥ ዙሪያዋን
ፍትት ፍትት  ፍትትትት ሻሿን
ሙልጭልጭልጭ ውስጥ ልብሷን
ብቅ ጥልቅ ብላ ጥልቅ ራቁቷን፤
እኔም ዐየት - ዐየት መንገዱን
ገረፍ ገረፍ - ደሞ ገረፍ ወንዙን
እቴትዬ ዕርቃኗን የምትንቦራጨቅበቱን፤
ጸጉሯን ወደ ኋላ እየሳበች እየጐተተች
ጡቶቿን ለፀሐይዋ እየሰጠች እየለጠጠች
ኋላዋንም ነካ ነካ - ነካ እያደረገች
ስትጫወት እያሾለቅሁ አየት......አየት
ደሞ መንገዱንም መልከት......መልከት፤......
ታድያን ዛሬ በጉርምስና ዘመኔ
ያ የጥንቱ ትይታ ተመልሶ መጣ ካይኔ
የረሳኋት እቴቴ
ብኸ ትልብኝ ጀመር ከፊቴ፤.....
ወንዙ ውስጥ ስትንቦራጨቅ

ጸጉሯን ወደ ኋላዋ እየሳበች እየጐተተች
ጡቷን ለፀሐይዋ እየሰጠች እየለጠጠች
ኋላዋንም ነካ ነካ - ነካ እያደረገች፤......

# ላንቺ ለጨለማዋቱ

ፀሐይዋ ሳትወጣ
በጽድቅ ጨለማ
  ፈልጊልኝ
  ታገኚኝማለሽ፤
መልኬ ባይታይሽ
በጣቶችሽ ዳሰሽ
ጠረኔን አሽተሽ፤
  ሌቱ ከነጋማ
  እኔም ያንቺ አይደለሁ
  አንቺም የኔ አይደለሽ።

# ልጅነት

ጊዜ በጊዜ ቀለበት
ሰተት።
አይ ያቺ የዘመን አምባ
በብይ ድብደባ
በኳስ ጥብጠባ
ባውጥ ለቀማ
ተጣባ፤
ደሞ ትንሽ ተገን ለአበባ
በጉርምስና ፍሬ እምታነባ።
ቢራቢሮ ማባረር ማባረር
ከቀለም ቀለም መሽከርከር
ለማሳደር
ለኮርሞ
አባ ጨጓሬ መሰል ነገር።
መች ጠፋችሁ
ጓደኞቼ
ካባ አልባሾቼ
እንደ ገዛኝ የልጅነት ሥልጣናችሁ?

የሕፃንነት ሞኝነት

የዐዋቂ ብልጠት

ዙሪያ ቀለበት

የሕይወት ጉዞት።

ቋታችሁን ለመሙላት

ሥጋት

ሥፍር - አችሁን ለመመጠን

ብክን፤

ዳገት - በረዶ መቧጠጥ

መፍረጥ

ጋት ለመቆንጠጥ።

በዛን የልጅነት መክሊት

ዛሬም እንነግድበት

ብቻ አንሶ ሲመነዘር

መንፈራፈር

ልብን በሲቃ ማንጫረር፤

መንገድ ብቻ - እግር ሳይኖር፤

መዳከር

በልብ ጫማ መውተርተር።

ላለመለምለም መብቀል

ላለማፍራት መተከል፤
    ተስፋ ቅርስ
    ምኞት - ውርስ
    በግብረ - ጠል
    እስቲል ከንበል።
አልፋ ኦሜጋ የሕይወት
    ልጅነት
ሲያረጁ ሲያፈጁ
    ከደጁ
ከልጅ ልጅ።
ዙሮ ዙሮ ከልጅነት
ኑሮ ኑሮ ከመሬት
እንደ ማለት።
ጊዜ በጊዜ ቀለበት
    ሰተት
አይ ያቺ የዘመን አምባ
    በብይ ድብደባ
    በኳስ ጥብጥባ
    ባውጥ ለቀማ
    ተጣባ፤

ደግሞ ትንሽ ተገን ለአበባ

በጉርምስና ፍሬ እምታነባ።

# ወለምታ (የወዳጅነት አባዜ)

አይጥፋ እንጂ አይውጣ ከእጃችን

ያለ ዐዋይ እካልቀረ ሙዳያችን

ወዳጅነት - እሚያሰናክል ሀብላችን፤

መዳቡ አልማዝ ፈሩ ወርቅ

የነብስ ብርቅ የሥጋ ድንቃድንቅ፤

እብስ ሲልም ድንገት፥ የፍቅር ሌባ ልሶት

እግዚኦታ አይመልሰው፥ ጾም ወይ ጸሎት።

ሩቅ አድማስ

በዐይን አይላስ፤

አእምሮ ከንዱን ባያጥፍስ

ምን ሊዳብስ?

ይበናል

አሻራው ይጠፋል

ውሉ ያለውል ይፈታል

የተካየዱት ቃል ኪዳን ሳይካየዱት ይወድማል።
ሙጫነቱ ማቅረብ ማቆራኘቱ
ባንድ አዋዶ ማጓተቱ
የልቦናን ድንበር ቀስ በቀስ ማስፋቱ
እያደር ያንሳል ግምቱ
እያደር ይሆናል ከንቱ።
የሕይወት እልፍ ሺ እጆች
ያበሩልን እልፍ ሺ ችቦዎች
በአጋጣሚ ነፍስ በቅጽበት ሽውታ
እልም ይሉ ጭልም
ደቂቃ ዓመታትን ድል ስትመታ
ገጠመኝ ገጠመኞችን ሲረታ።
እና ለዚህ ነው፤
ትንሽ ሽንቁር ትንሽ ስብራት
የመርፌ ቀዳዳ ስፋት ያላት
ከፍቅራችን ብትሠርጽ ብትወጣ
ልቤ ጨጐጊት ያወጣ፤
አባቶች እንዲሉ
ውሾች በቀደዱት ጅቦች ይገባሉ።

## ያባትህ ልጅ

አሁን እንዳንተ ማን ሊመጣ

አባቱን መስሎ የወጣ?

እንዳንተም ያባቱ ልጅ የለ

ጥበብን አቅፎ የገደለ

አወፍሮ ያሰለለ፤

አንድም አንተን መሳይ - አባቱን መሳይ የለ።

አባትህ

በግዕዝ አጥር ንፉግ ሕይወቱን ቀጽሮ

ከመላእክት ጋር ታፍሮ

ከሰማዕታት ተተራሩጦ

ከመናፍስት አግቦ ገጥሞ፥

ያድባር ያህል ተፈርቶ

ካድባር ይልቅ ጐልብቶ

አሸለበ፣ አንተን አምሳያ ልጁን ተክቶ።

አባትህ

የቋንቋው ካዝና የምስጢሩ

ስውር፥ የእንቆቅልሽ ድርድሩ

የመደርጀቱ ተአምር - እኩይ ግብሩ።

«በምድረ በዳ የሚጮህ ድምፅ»

ሐያሲ - የራዕይ ቅርጽ

በእሳት ልሣን ተናጋሪ
የመለኮት ቃል ፈካሪ፣፤
  አባትህ
    ሰደድ እሳት ምላሱ
    አይፈታ ጥበብ ቅርሱ
    አይገለጥ ምስጢር ውርሱ፤
    ደሰስ ይበለው - አንተን አደረሰ እምታደርሰው
    አንተን ወለደ እምትወልደው።
    ከሕይወት፣ ወዲያ ላያልፍ የጥናትህ መደቡ
    ከሕዝብ ጉያ ላይርቅ የምርምርህ ክበቡ
    ምን ብትረቅ ምን ብትርቅ እምትደርስበት ግቡ
    ወይ የመነሻህ እርካቡ፤
    የስንቱን ዐይነ ልቦና አታለልክ
    አስተዋይነቱን አጭበረበረ
    እንዳባትህ - በቋንቋ ግርዶሽ እየተጠለልኩ።
    በጆሮህ ጥጋት ላንሸዋሸው የአፍርንጅ ልሳን ነፍስ
    እባከንክ ዕውቀት ምርካት -
    እንዳይደርስ ከሕዝብ አእምሮ ምላስ።
የዋህ ፍሬ ነገር በባዕድ ቋንቋ ተሞሽሮ
በሐሰት ግርማ ሞገስ ታፍሮ

በኔነት ትዕቢት ተጫፍሮ
ለየህ፤ ከሕዝብ ደማቅ አደባባይ
ገደመህ፣ በሱባኤ ከብቸኛ ምስካይ።
እማያውቁትን ይፈሯል
እሚፈሩትን ያከብራል
ሲባልማ ሰምተህ ይሆናል።

አባትህ

ራሱ በማይፈታው እንቆቅልሽ፥ ተረብ የድግምት ወጀቦ
ፈውስ እያለ ሲያደባይ፥ የስንቱን ሰው ቀልብ ሰልቦ፤
ሰዊራ - አሽዊራ - ኑሽዊራ - አቁራ - ነቂራ
አዝቢራ - አዥበርበቢራ - አጽቢራ - አጽበርቢራ
ሐሊላ ላሒል ቃኢል ባኢል ናኢል
ባባባላላፊፊፊፊዳዳ - ሀሀሀ (ሀ - ሀ - ሀ!)
አንተም የመዘለፊያ እጅ ዛቢያ
ዘመናይ ደብተራ ዐባያ
ተጠበኩ ስትል ጠበብክ
ዐወቅኩ ስትል ደነቆርክ
መቅረዝ ሲሉህ - እንቅቡም አንተው ሆንክ።
እና ከአባቴ የተለየሁ ነኝ።
እያልክ ብትለፍፍ ብትቃጅ

ሥራህ ይታዘብሃል መሆንህን የሱ ቅዳጅ
የመንፈሱ ንድፍ ወረቀት
የገዘፈበት መስታወት
የደመቀበት መጽሔት።
ኧረ ካንተ ወዲያ ማን ሊመጣ
አባቱን መስሎ የወጣ
እንዳንተም ያባቱ ልጅ የለ
ጥበብን አቅፎ የገደለ
አወፍሮ ያሰለለ
አንድም አንተን መሳይ - አባቱን መሳይ የለ።

# የንፋግ ምጽዋት

ያን የዘመን ጉዲፈቻችሁ፤
ያደፈረሰ ዐይናችሁን
ያቀጠነ ድምፃችሁን
እባካችሁ፤ አላምዱን ፍርሃታችሁን።
    ያን ቀን ኦቶብሱ ላይ
    ስትሣፈሩ የሆነውን ሳይ
    ከአንቀልባው እንደ ሾለከ ጨቅላ
    ነብሴ ጮኸች ከሾህ ተንጋላ።
ደማቅ ሰማያዊ ቦጌ ታጥቀህ
ጭስ መሳይ እጀ ጠባብ ለቀህ
ኮት ብለህ ዕድፍ ደርበህ፤
በግራ እጅህ ከዘራህ
በቀኝህ የልጆችህን እናት ጨብጠህ፤
ገባ ስትል «ወንድምዬ» የሌላው ዐይንኮ ገላመጠህ!
ኮስታራ ገጹ ገረመህ፥
በሹክሹክታው አንተን ለየህ፥
አትጠጋን አትቅረበን አለህ!
ከፊቷ አንገቷ ጠቁሮ፥ ደረቷ ጠቁሮ

እግሯ በንቃቃ ተቦርቡሮ፥ ተሸርሽሮ

ቦብሊን ሸንሽና ለብሳ

በላዩ ዶቃ ነገር፥ ጨሌ አፍሳ

ጸጉሯን በቅቤ አርሳ

ጮጮዋን እንደ ጨበጠች፥ የት ትቀመጥ፥ የት ታኖራት?

እንደ ላስቲክ እየሰፉ ቦታውን አጠበቡባት፤

በልብሷ ተጠየፏት።

በጠረኗ ተሰቀቋት።

እስቲ በል፥ ይህችን እናት

የሀገር እናት የት ታኖራት?

ካርኒ ቆራጩ የተግባር ቃሉን ነፍጓችሁ

ቀና ድምፁን ደብቋችሁ።

ኋላ ወስዶ፥ ከዕቃ ጋር ሲወሽቃችሁ፥

አሳዘነኝ አስለቀሰኝ መራቆታችሁ

ዐልፎ ከእድፋም ልብሳችሁ።

ግን የኔ እንባ፥ አልጠፋኝም እንደሆነ የይስሙላ

የንፉግ ምጽዋት ዘለላ።

ወይ የቅንጦት ወለላ።

እናንተ እንጂ፥ እናንተ እንጂ ወዛችሁን ያነባችሁ

እናንተ እንጂ፥ እናንተ እንጂ ሰቀቀኑን የቻላችሁ

.......ዳፈን፥ ለታሪክ ዋስትና የከፈላችሁ።

# አዬ የኔ ዝምታ ጋግርት

አዬ የኔ ዝምታ ጋግርት
አይወለድ ቃል - አጥንት።
በከተማው በገጠሩ
በአምባው በሸለቆው በዱሩ
በየቀኑ በየዕድሩ
ኡኡታ ሲቀጥል እሪታ
ፍጥረት ባንደበት ሲማታ፤
ሆን ብዬ በጆሮዬ ላይ ተኝቼ
የልቤን ወያኔነት ቀጥቼ
ፍርሃቴን - አብሮ አደጌን ተማጥኜ
እኔው የኔኑ ድምፅ ተሡቅቄ
እኔ የኔኑ ልሣን አፍኜ፤
ሲጐነትሉኝ ጸጥ እርጭ
ሲነካኩኝ ጭጭ ምጭጭ።
አዬ የኔ ዝምታ ጋግርት

አይወልድ ቃል - አጥንት።

## ልጅቱ - የዘመነችቱ

ልጅቱ - የዘመነችቱ
ጧቱን ብድግ ንሥት
　ትለውና
ፈቷን ትጥብ እሽት
ፍትግ ፍትግትግ
ዱሩላዋን ልቅቅ ጥፍት
ሌላ ምናምን ዱቅት
ሽፍሏን ቅልም ጥቁርት
ከንፈሯን ቅብት ቅልት
　ታደርግና፤
ልጅቱ - የዘመነችቱ
　ሱሪዋን ለምምቦጫሙኡን - ሱርት
　ጫማዋን ነጠላውን - ጭምት
　ቀበቶውን ሰፊውን - ቅብትት
　ጃኬቷን የቆዳውን - ጅክት

ታደርግና፤

ልጅቱ - የዘመነችቱ

መስቷቱ - ትልቁ መስቷት ፊት

ትቆምና፤

ሣቅ ግጥጥ......ሣቅ ግጥጥ.....ሣቅ

ደርሶ ፍልቅ........ፍልቅልቅ......ፍልቅልቅ

ከንፈር ገጠም.......ደሞ ከፈት......

ደሞ ገጠም.....ገጠምጠም

ወደ ኋላ ሒድት......ሒድት

ደሞ ምልስ........ምልስ.......ምልስልስልስ

ሽንጧን ሰበር.........ቅልስ.......ቅልስልስልስ

ዳሌዋንም ውዝ ውዝ

ቂብ ቂብ......ቁንን ቁንን

ክው ክው.......ጅንን ጅንን

ደሞ ፈገግ......ደሞ ቅጭም.....ቅጭምጭምጭም

ዐይኗን ከፈት.......ደሞ ጨፈን......ስልምልምልም

ደሞ ጉርጥ.......ደሞ ጥቅስ......ደሞ ጉልጉል

(በራሷ ትቀልድ ይመስል)

ልጅቱ - የዘመነችቱ

ፕሮቫው ብሎ ጥቅልል

ወደ ቁርሷ መለስ ስትል
እማማዋ ንድድ ቁጥጥ
ትንሽ እህቷን ጥርት
በኩርኩም ግጭት!
«ገና ካሁኑ ይወጣብሽ
ለምነው ጧት መነሣትሽ?»
ደሞ ማለት።
አባባዋም እዝን ቁጭት
ጸሎታቸውን ዝንግት
«ወይ ጉድ መበላሸት»
አርዝመው እያዩ ማለት።
ልጅቱ - የዘመነችቱ
ገብሪ ገብሪ እያለች
እማማዋን እያሣቀለች
አባዬዋን እንደ ቦረሠች
ላስቲክ ብጤ ነገር ባፍዋ እያላመጠች
እያንቀጫቀጨች
ፍርድ ብሎባት ችኩል ችኩል እያለች
እሑድ ጧቱን ባንድ ሰዓት ውልቅ ያለች
(አፍታም ሳትቆይ - ወድያውኑ)

ሰኞ ጧቱን ምልስ ትላታለች።
ልጅቱ - የዘመነችቱ።

# ስንብት

ዋ! አንቺ የምኞት አጥናፌ
የየዕለት ራዕይ ንድፌ
የአለኝታ ምዕራፌ
    ሁነትሽን ጠላሁት
    ኑሮሽን ተሠቀኩት
የማትጨበጨ ጉም
የሕልም ሕልም ሕልም።
ሔጄ ሔጄ ፈለግሽን ተከትዬ
ጉልበቴን አባክኜ ቅስሜን ጥዬ
እንደገና ወደ ኋላ......ወደኋላ
ከቁም በድኔ ጥላ
ከዕንባዬ ከለላ።
እስቲ እዩኝ አስተውይኝ

ባይኖችሽ ጨረር ሞሽሪኝ
በጥዑም ዜማሽ አዛንጊዝኝ
በቃለ ልብሽ አጽናኚኝ፤
ብልሽ ለማታደምጪኝ
በነበልባልሽ አቃጥይኝ!
ግድየለሽም ተይው ይቅር
ላልተጋባን እንዳበል
ላልተኳኳን እንዳለል።
እስቲ እባክሽ፤ ለሞቴ ልማፀንሽ
የመንፈሴ ቦግ ቦግታ ጠይሞ
የተስፋዬ ተግ ተግታ ተስለምልሞ
እባክሽ፥ ላልኖርኩኝ አታቁሚኝ
እባክሽ ላልሞትኩኝ አታስተኚኝ።
ታሪክ አይደል ገድልኮ ነው እሚጻፍ
ካንድ የዕድሜ እንጓ እስከ ሌላው ጫፍ
ተከትዬሽ ስውተረተር ከስንፍ እስከ አጽናፍ፥
መስሎኝ ፍቅርሽን ብቻ ያመለኩ
ውዳሴሽን ያነበብኩ
በራሴ ላይ አስማት ደገምኩ
   መተት አዞርኩ።

በይ ስንት ቀን

ስንት ቀን ባንቺ ሰቀቀን

ባንቺ ላይ ያለኝ እምነት ባንቺ ላይ ያለኝ አለኝታ

እንደ ሰዓት መሙያ ጊዜ እየቆጠረ ይፈታ?

ግዴለሽም ተይው ይቅር

ላልተጋባ እንዳበል

ላልተዳኋን እንዳለል።

ምነው ዞትር በሩቅ ሣቅሽ መጠውለጌ

ምነው ሁሌም በሩቅ ዳናሽ መበርገጌ

በርቂ መዓዛሽ መግተርተሬ

ላይለወጥ ዕድሌ ላይለወጥ ዕድልሽ

ላልወጣ ከክበቤ ላትወጪ ከክበብሽ?

ለምን ፋይዳ ወፍ ሁኜ መዘመሬ

  በጐጆዬ ተጠፍሬ

የዕጣችን ግንባር - ገደል

  ላይደለደል።

ላያመጣሽ ጕርፉ

ላያጉዘኝ ዶፉ

አፋፉ ላይ ቆሜ

ላይቃና ስቡር ቅስሜ፥

ላላፍር ከዕድሜ ልክ ሕመሜ
ላይሻለኝ የጣር ዘላለሜ።
እባክሽ ተኚይ
የዋህ አማኝ ብለሽ ማሪኝ
ጅል አፍቃሪ ብለሽ ናቂኝ።
ጽድቅሽን ብዬ ኩነኔ
ፍቅርሽን ብዬ ምናኔ።
ድንገት የወረደ አሎሎ
እንደ መብረቅ ከንድ ተገንጥሎ
እንዳከሰስ አቁስሎ
ተበቀልሽኝ፥ ስም ሳይኖረው ለበቀሉ
ገደልሽኝ፥ ወንጀይ ሳይኖረው ለበደሉ።
ግዴለሽም ተይው ይቅር
ላልተጋባን አንዳበል
ላልተኳኳን ንዳለል።
ብቂኝ፥ በሕሊናዬ አድማስ አትታይ
ልገላገል፥ ከትዝታሽ ከጭብጥሽ ሥቃይ
ከመስለምለሜ ብካይ።
ደኅና ሁኚ........ደኅና ሁኝ በይ
ኮከቢቱ የሰማይ እንጉዳይ

የፐሎቶ ላይ ሲሳይ

ዱድባይ።

# ፀሐይን ላያይ ተፈጥሞ

ሲንደረደር ሲንደረደር

ወደቀና ካንቺ ድንበር

ካንቺ አምባ ካንቺ መንደር፤

አይነሣ በምን ዐቅም፥ በምን ሰበብ

የወግ ገደብ?

ቢቸግረው በሩን ዘግቶ፥ እግሮችሽ ላይ ተደፍቶ

ሲልሽ ‹ሁኚኝ - ያንቺ አድርጊኝ›፥ መላ መንፈሱን አካቶ

ከዘመድ ዐይን ተገልሎ፥ ካለፈ ሕይወቱ ተፋቶ

በ‹እግዜር ቢል ነው› አንደበቱ ቅሬታውን አዘናግቶ

ባንቺ ቆሌ ውሎ አደረ፣ ባልፎ ሒያጅ ፍቅርሽ ረግቶ።

ምንም ዐልፎ ሒያጅ ፍቅርሽ ቢሆንበት፥ የሰንበሌጥ የሣር ባላ

ምንም ፈገፍታሽ ቢጨልምበት፥ ምንም እያደር ውልሽ ቢላላ

አዚምሽ እንደሁ ወድቆበታል፥ አያልፉትም ያንቺን ኬላ።

ወረቀት ላይ ያልነጠበ፥ ቃል አለበት አንዳች መሐላ።

እና ነበልባሉ የከሰመ፥ ዐመድ ብናኙ የቀረ

ገለባው ብቻ የኖረ፥ አሠሩ ብቻ የተከመረ

ስብዕናው የጮረረ፥ የነበር ግቱ የነጠፈ

መሆኑ ቅር እያሰኘው ከጭብጥሽ እስካላለፈ።

የከፋት ጽድቁን ነው የሚሻ፥ አይወገሽ በመግደርደርሽ

አይበረግግ በወረትሽ።

በሲኦልሽ ሲኦል አካብቶ፥ ጨለማሽን አጨልሞ

አለኝታውን አካቶ፥ በተስፋ መቁረጥ ከርችሞ

እዋሻሽ ተቀብሮልሻል፥ ፀሐይን ላያይ ተፈጥሞ

ፀሐይን ላያይ ተፈጥሞ።

# ሽር በይበት ሽር

ሽር በይበት

ሽር በይበት ሽር በያውራው ጐዳና

በየኮሪደሩ በየቢሮው ካዝና

በየስርጓጉጡ - በየስርጣስርጡ

በየጉጥጉጡ በማጡ በድጡ፤

ሽር በይበት ሽር

ሽር በይበት ሽር ከጓዳ - አደባባይ

ከታሕት እስከላይ

በዝንተ ዓለም ፍና በለሆሣሥ ዳና

በባህል ዳዋ ውስጥ በፍጡር ገበና፤

ሽር በይበት ሽር!

ያንቺን እግሮች እሚያስር ሰንሰለት ካቴና

የቀጠቀጠ ጣት የፈጠረ ሕሊና

ቢሹት ቢሹት ቢሹት

ይኸው እስከ ዛሬ አልተገኘምና።

# ዘመዴን ስስመው

ዘመዴን ስስመው
ጉንጩ ቢሻክረው
እኔንም ሻከረኝ፤
ዕድሜ መለስለሱ ማብቃቱ ታወቀኝ።

# አንተን በመኻል ኢያሳጣኝ

አንተ ነህ ጓደኛዬ
የምሥጢር ጌጥ ሙዳዬ
(የብል ማከማቻዬ)
አንተ ነህ ጓደኛዬ።
ሌላም ጓደኛ ኢያሻኝ
አንተን በመኻል ኢያሳጣኝ።
አንተ ንቁ ብርቱ ማግኔት
እኔ ሌሎች የግራ ቀኝህ ብረት።
ባንተ ዐልፈው ነው እሚያዩኝ
ባንተ ዘልቀው ነው እሚሰሙኝ

አቦ አንተን አያሳጣ
ሌላ ጓደኛም አያሻኝ።
አንተ ሠናይ፥ የዜማ መምህር
ዘፈኔን እምታንጐራጉር
አንተ ብርቱ ባለ ቅኔ
ዘራፊ የስንኝ ውጥኔ
አንተ የኔ ስማበሎ፥ አንተ አፈእኔ
ቁንጣኔን የምታስታግሥልኝ ጠኔ
መለኪያዬ - የዐረብ ቤት ሚዛን
ካጠገቤ እማትለይ የመከራ ቀኔ።
ሌላ ጓደኛም አያሻኝ
አንተን በመኻል አያሳጣኝ።
　　ወደኔ የሚፈሱትን ወንዞች ከትርልኝ
　　ኩሬ እንጂ፥ ባህርኮ አይደል በልልኝ
በደግነቴ እንዳልጐዳ፥ እዚያው ባሉበት እቆይልኝ።
　　ታጠርልኝ፥ እሾህ ሁንልኝ አሜከላ
　　ገድመኝ፥ በአሉባልታ በድለላ
ቀጽረኝ፥ በጠብ በሐሜት ኬላ
ለኔ ስትል ክፉ ሁንልኝ
ደግነቴን አታውራብኝ።

ሌላ ጓደኛም አያሻኝ።
አንተን በመኻል አያሳጣኝ።

## አለ፥ ‹ጠና በል› እሚለኝ

የብቸኝነት ጥምቡሳሱ
የፍርሀት ግሳንግሱ
በበረዶ እጁ ሲዳስሰኝ
በእሾህ ጣቶቹ ሲቧጥጠኝ፤
ምላስ ከፍነሬን ሰብስቤ
ዐይነ ሕሊናየን አድቤ
ከመታመቁ ከወላፈኔ
ከማቄ ከሰመመኔ፤
ሰንበሬን አመሳስዬ ከኮከቤ፤
የብቸኝነት ጥምቡሳሱ
የፍርሀት ግሳንግሱ
እንዳልተነገራ ፈረስ ሲያደባየኝ
እንደ ደራሽ ውሀ ሲአይፍነኝ
እንደ ተጋለጠ ሐሜት ሲሰብረኝ፤

አለ፤ በርታ ጠና በል የሚለኝ።

በዐይኔ እንባውን አፍሶ

በምላሱ ምሬቴን ላልሶ

ማቄን በካባው አለሳልሶ፤

ከዋሽንት ፉጨት ጨርፎ

ከቅኔ ስንኝ ጠልፎ

ከፉጨቱም ከስንኙም ጨምቆ

ከውበት እዝን ሰንቆ

ቀስተ ደመና አርቅቆ

በርታ፥ ጠና በል እሚለኝ

አለ፣ እሚያስተዛዝነኝ።

የብቸኝነት ጥምቡሳሱ

የፍርሀት ግሳንግሱ

በበረዶ እጁ ሲዳስሰኝ

እንደ ደራሽ ውሃ ሲያፍነኝ።

# እሱ ነው - እሱ

እሱ ነው - እሱ

ዐይን ባይኖረው

ለምን ብርሃን ኖረ እሚለው፤

እግር ባይኖርው

ለምን መንገድ ኖረው እሚለው፤

እሱ ነው - እሱ

ከቀናቴ

ፀሐይቱን የሰረቀ።

በመንገዴ

አሜኬላ ያጸደቀ።

ድኅረ አብዮት ግጥሞች

# ዛሬን እንኳን

እስቲ ዛሬን

ዛሬን እንኳን

ዛሬን እንኳን ሣቂ፤

እስቲ ዛሬን

ዛሬን እንኳን

ዛሬን እንኳን ፍንጭትሽን አትደብቂ፤

አትደብቂ - ፈገግታሽን አትፋቂ

ጐረቤት ይታዘብሽ

የሐሴት ደመኛ አያርግሽ

እባክሽ፥ እናት ዓለም አባክሽ

የዕጣሽን አድማስ ጉም ሽፍኖት

ምድር - ሰማይሽን አጨልሞት

ፀሐይሽን ቢጦልብሽ

ጨረቃሽን ቢሠርቅብሽ

ጨረቃሽን ቢሠርቅብሽ

አንቺ እማዬ እንደ ሌሎች፥ መሣቅን እማታውቂ ነሽ?

በዕንቁጣጣሽሽ ዋዜማ ድንኳን

በተቀጣጠለው ችቦ ውጋጋን

ፈካ ይበል የገጽሽ ብርሃን
ደመቅ ይበል የልብሽ ዙፋን
ዛሬን እንኳን፥
 እማምዬ
   ዛሬን እንኳን።
ለኛም ችቦ አዳርሰሽን፥ ኢዮሃ አበባዬ እንበል
በውሃ አይደል፥ ዛሬስ በቃል በሁካታ እንጠበል።
ተቸንክሮ እንደኖረ በር፥ በትግላችን ተለማምጠን
አንደበታችንን ተማጽነን፥ ከንፈራችንን አላቀን
ቢጐለድፍ ምላሳችን፥ ባይጥም አንኳን ዜማችን
ቢሰባበር ድምፃችን ዝርው ቢሆን ነገራችን
ብቻ አንጨህ ፍቀጅልን - ጩኸት ነው እኛን ያማረን።
እውን ጩኸት ነው እኛን ያማረን፥ በጩኸት እንንበልበል
የገደል ማሚቶ ትንቃ፥ ከእንቅልፍ ትራሷ ትከንበል
ከቦዘን ሕልሟ ትፈንገል።
አንደበታችንኮ ዝጓል እማምዬ፥ አዕምሯችንን በክሎ
ቃል አስጥሎ ሐሳብ ገድሎ
ያይንን እውነት በአርምሞ አሰልስሎ
የጆሮን ታሪክ በዝምታ አብጠልጥሎ
አንደበታችንኮ ዝጓል እማምዬ፥ አዕምሯችንን በክሎ

የጣር ይጭንቅ ድምፃችን፥ እንደ አምኃ ዛሬ ይድረስሽ
የዘመናት ቅርሳችን፥ ወጥቶ ፊትሽ ይቅረብልሽ
የፍሬያችን የምሥራች ከቶ ምን ቢሆን አንነፍግሽ።
ከኛ ፈገግታ አትጠይቂ
ከኛ ሐሴት አትጠብቂ
እንባም ለኛ ተስፋ ነው፥ እባክሽ ስለ እንባችን አንቺ ሣቂ።
    አንቺ፥ ስለ ጩኸታችን ፈንድቂ
    አንቺ፥ ስለ ጭንቅ ድምፃችን ቦርቂ።
አለመሣቅኮ ይቻላል፥ አለማልቀስ ነው ጭንቁ
የመንፈስን እንጉርጉሮ፥ በመንፈስ አምባ ማመቁ
ውስጥ ውስጡን እየደሙ፥ በቀቢፀ - ተስፋ መድቀቁ
ለተስለመለመች እውነት፥ የደም ደብዳቤ ማርቀቁ
በቅሬታ ሰደድ እሳት፥ ሕዋሳትን መጨፍለቁ፤
አለመሣቅኮ ይቻላል፥ አለማልቅስ ነው ጭንቁ።
እና፤ እስቲ ዛሬን
    ዛሬን እንኳን
    ዛሬን እንኳን ሣቂ፤
እስቲ ዛሬን
    ዛሬን እንኳን
    ዛሬን እንኳን ፍንጭትሽን አትደብቂ፤

አትደብቂ - ፈገግታሽን አታርቂ።

# ብቻ መገኘትሽ

እንደ ናፋቂ ሕፃና እናቱን እንዳየ
በደስታ ሐዘን እንደ ተሠቃየ፥
እንባውን እንዲያዘንብ ለሐሴቱ መቅድም
ዐይንሽን ባየሁኝ እንባዬ ባፈስም፤
ወኡ፤
ታውሮ እንደ ኖረ እንደ አንድ ጐበዝ
በድንገት ብልጭታ እንዲደነዝዝ
በጨለማ ቤቱ አንቺ ጮራይቱ
ዘው በማለትሽ ቢጠፉኝ ብልሃቱ፤
እንባውም ይደርቃል
ብልሃቱም ይገኛል፤
የወጣሽው ፀሐይ ጽልመቱ ሲሸሽ
ብቻ መገኘትሽ
ብቻ እምኖርሽ።

# ሐዘንሽ አመመኝ

ውል አልነበረኝም የፍቅር ቀጠሮ

ቃልም አላኖርንም በወግ ተቀምሮ፤

እኔ አንቺን እንዳላይ

አንቺ እኔን እንዳታይ አምባችን ተቃጽሮ

ዕጣችን ተካሮ፤

ቀለምሽ ከዐይኔ አሻራሽ ከጣቴ ባይጠፋ ተማትሮ

(እትብት እምብርት ሁኖ እንዲኖር ደድሮ)

ይኸው አካየደን በድንገት ዘንድሮ።

የገጽሽ ብርሃን ቢጠይቅም ፀዳሉ

ድምፅሽ ቢቀጥንብኝ ቢሠልብኝ ቃሉ

ወዘናሽ ቢማስን ዛሬ ያለውሉ

በእጆችሽ ጨበጠኝ ሐዘንሽ ሥዕሉ፤

ሐዘንሽ አመመኝ

ብሶትሽ ጠቀሰኝ።

ጀንበር ነሽ አበባ ሕይወት ተስፋ ዘቦ

ፋሲካ ዕንቁጣጣሽ ማኅሌት ገንቦ

ብዬ ያወደስኩበት ታዘበኝ ዘመኔ የትላንታት ቀኔ

ዛሬ ሊጮህብኝ ቅኔ እዳይደል እውኔ፤

ሐዘንሽ አመመኝ
ብዞትሽ ጠቀሰኝ።
የገደል ማሚቶን ታዘብኳት ተኝታ
በጩኸትሽ ማየት አኩርፋ ታክታ
ላንቃዋ ይታየኛል ደም ለብሶ ደም ጐርሶ
ቃልሽ ያለፈበት በጭንቅ ተለውሶ፤
ሐዘንሽ አመመኝ
ብሶትሽ ጠቀሰኝ።
ጽጌያቱ ደረቁ ንቦችሽ አለቁ ሰዎችሽ ደቀቁ
ጨፌ ላይ ተኝተው ባድማ ላይ ነቁ፤
ዐዋይን ሰማኋት ስታለቅስ በይፉ
ከጐጆሽ ስትወጣ ትቢያዋን አራግፋ፤
ሐዘንሽ አመመኝ
ብሶትሽ ጠቀሰኝ።
አላውቅልሽ ብዬ አታውልቂልኝ ብዬ
እምነትሽን ጥዬ ፍቅርሽን ገድዬ
አኩርፌሽ ስቀመጥ ያው እንደ ባላንጣ
ይኸው ነጭ ማተብሽ ሊያስታርቀን መጣ፤
ሐዘን ነው ውበትሽ ውበት ነው ፍቅርሽ
ብርሃን - ጥለት አልቦ ከል ነጠላሽ

ዐይኔን የገለተው ጥቁር ጨለማሽ፤......

ሐዘንሽ አመመኝ

ብሶትሽ ጠቀሰኝ።

# ለድንገት - በቀል ፈላስማ ዐርበኞች

ታዲያ ዛሬ፥ በሰበብ ባስባብ ሰንሰለት

ተጋምደህ ብትሚገት

ብትቋሰል ብትዛበት

ብትናፈር እንደ ርጥብ እንጨት

ብትዳቆስ እንደ መርግ ንደት፤

ታዲያ ዛሬ፥ ባደባህበት አደባባይ

በነገር በተረብ ሥራይ

በደባ በሾርኒ ግዳይ

ልግነን ስትል - ብትፋረስ ብትጣጣል ብትሻወድ

ልድመቅ ስትል - ብትንኳሰሰ ብትማገል ብትፏደድ፤

ታዲያ ዛሬ፥ የወግ ጽዋ ብትጣጣ

ብትፋታ ብትዳበል ጦጣ ለጦጣ

በቋንቋ ብትናገድ፥ ብትቧደን በአፍ ደፈጣ

እንደ ርችት ብትንጣጣ፥ እንደ ፍግ የትም ብትሰጣ፤
ታዲያ ዛሬ፥ አስተናግር እንደ በላ
ሺ ምላስህን ብታቋላላ እልፍ ትናጋህን ብታላላ
ሸካራው ልብ - አንደበትህ፥ በአራራይ ዜማ ቢሰላ
ለማኙን ቀርቶ ጥላውን፥ ለማቀፍ እጅህ ቢያደላ፤
ካልሆነ፥ የታሪክ ሐቅ አምኖ፥ ይቅርታውን ለመማጠን
ካልሆነ አጉራህ አጠናኝ ብሎ በአዲስ ፍኖት ለመፋጠን፤
ማነህ በአቻምና፥ በአቻምና በስቲያ
አዳፍነህ የእምነትን ቋያ
ነብስህን ከተህ በወኔ ጉያ
ለዐይንህ ዐይን፥ ለአዕምሮህ አዕምሮ፥ የሰጠህን ባለ አምሃ
ረስተኸው ርቀኸው ድንጋይ አልብሰኸው በበረሃ፤.......
የፍርድን ጩኸት አቤቱታ
የማወቅን ሕመም ቅሬታ፥
ሕሊናን በማባበል
በየምናምኑ በመደለል
ያላዘናጋህ ያልተዘናጋህ
ማነህ? እስቲ ማነህ?
ከማይመስሉህ ተቧድነህ፥ ባንድ ሠምረህ
ኩኩሉ አልነጋም፥ አይነጋምም ብለህ

ለፊውዳል ቅኝት ነዝረህ፥ ለቡርዧ ከብሮ ተደልቀህ

ለኔነት በኔነት ማራቶንተጣልፈህ

ለክብር ለንዋይ ተዳፍተህ

ለስም ለዝና ተዳምተህ

ነቀዝ እንደ በላው እህል ቀለህ

ዋግ እንደ መታው መኸር ሻሽረህ

መልሕቋ እንደ ጠፋ መርከብ ሰፈህ

የትም ነፍስህ.......የትም ባክነህ........የትም ደቀህ፤

የኔሮንን ሣቅ ያልሣቅህ

.......ማነህ፥ እስቲ ማነህ?

ካለህ፥ እኔ ነኝ በል.......በል

ላንተ ይገባሃል የሰማዕት አክሊል።

# ቋጥኙ

መሠረት ጽኑ

የብረት ምሰሶ ነኝ ባይ

ቋጥኝ በቋጥኝ ላይ፤

ንፋስ ራሱን ያዞረው

ሣር ቅጠል ድንጋይ ዐፈር

ስብርባሪ ነገር

ሲኮረኩመው እንዳከከው

ሲገፈትረው እንደ ዳሰሰው፤

(ትዕዝብቱ ብቻ እያሣቀው)

ግና አንዲት ጠብታ.....አንዲት ጠብታ

ውሃ ተሰኝታ

አፈር ስትነክስ

ድንጋይ ስትጐርስ

ውቅያኖስ

(መርከብ እምታፈርስ)

እና መች ቀረለት መነጠቁ

ከግርሽ ዳሱ መውለቁ

እንዲያ እንዳልተንከተከተ -

እንዳልሣቀ፤

ወደ ቁልቁል

ወረደ

ቋጥኙ

እየ

ተን

ሰቀ

ሰ

ቀ

## በትን ያሻራህ ዘር

በጓጥ በስርጓጡ

በማጥ በድጡ

እንደ ተንጋለልክ - እንደ ዘመምክ

ትንፋሽህን እንደ ቋጠርክ

ልል ቀበቶህን እንዳጠበክ፤

የተልእኮህን አባዜ

የሕይወትህን ቃለ - ኑዛዜ

ውርውር!
የእጅህን ዘገር።
በትን!
ያሻራህን ዘር።
ይዘኸው እንዳትቀበር።

# ትዝታን ማለስለሻ

አየሽ፥ አንድ ቀን ደሞ......ደሞ
የሔዱበትን መንገድ አዝግሞ
ይመጣልና ከርሞ......ከርሞ
ሲጋፈጥሽ ሲበርቅብሽ
ጭለማዬ ሲበርቅብሽ
ጭንቁ ገዝፎ ሲጋርድሽ
አትበርግጊ አይጸጽትሽ
ዝምታዬ ሲጮህብሽ።
ለቅሶ ትካዜ መብከንከን
ፍቅር ጥላቻ ሰቀቀን
ቅናት ቅሬታ መማሰን

ጨረር ላይኖር፥ በቀቢፀ ተስፋ ደን።

ተፈጥሮ ፍሬን አልቦ

በማጥ በስርጓጉጥ ተስቦ

አበቃለት ነዶ ከልቦ

በድንፋታው ተገጣጥቦ።

እና ለመውደቅ ለመንከባለል

የተፈጥሮን እሚያህል ገደል

    የት አል

    ብዬ ነው፤

    እኔው

የተበዳይ ይቅር ባይ ራሴው

እንባዬን ከዐይኖችሽ እማብሰው።

# ገና በልጅነት

ገና በልጅነት.......

ገና በልጅነት እርጅናውን ኖሮ

ገና በፍላነት.......

ገና በአፍላነት ከዕድሜው ዳር ተሻግሮ፥

ጀንበሯን ሲያስተውል

ቀለሟን ቸል ብሎ

ሙቀቷን አፍቅሮ፥

ጨረቃን ሲታዘብ

  ድምብል - ቦቃን ትቶ

  አበባዋን ጥሎ

  ብርሃኗን አንሥቶ፥

ገና በልጅነት.......

ገና በአፍላነት.......

ከብርሃን ከሙቀት ምስሉን ለመከወን

  ሐውልቱን ለማቆም

ሲወድቅ ሲነሣ ሲለፋ ሲታገል

  ሲጣጣር ሲደክም፤

ብርሃንና ሙቀት ሐውልት አልሆን አሉ

ቀለምንና አበባ ሳይከስቱ ኃብረው

ኃብረው ሳይሳሉ።

# መንታ ነው ፍጥረትሽ

ተገልተ ዕቶኑ ተከፈቱ ዐይኖችሽ

ብርሃን አዘነቡ፤

ቀለማት አቅርረው ውበትን አነቡ፥

ጋረዱት ኮከቤን ብርሃን አጠሉበት

ኩራዜን በማሾ አደናገዙበት።

ክንዶችሽ አቀፉኝ አቅፈው አባበሉኝ

አባብለው አስተኙኝ

ውጋቴን ነጥቀውኝ ቁስሌን አዘናጉኝ

ከሰመመን ጀርባ እሾህ ላይ ሊያነቁኝ

ቁርንጮ ሊያለብሱኝ በማቅ ሊፈትጉኝ።

ሰጠሽኝ ጨለጥኩት ወለፈንዴ ጽዋ

ባንድ የተቀመመን ማርና ግራዋ።

ምን ይሆን ፍጥረትሽ ጥንድ የሆነ መንታ።

ዋይታና እልልታ።

ያልቃሾች ሙሾ ነሽ የዕድመኞች ጨዋታ
የሐሴት ርችት የሐዘን እሩምታ።

# የቀበሮ ጉድጓድ

በቀበሮ ጉድጓድ ቀበሮ መስሏቸው
በቀበሮ ጉድጓድ ቀበሮ መሷቸው
ውሾቹ አጓሩ በዛ ጩኸታቸው
እየሩን በከለው
ምድሩን አገረኘው - ትፋት ድንፋታቸው!
አይ የውሾች ነገር፥
ማን በነገራቸው
ማን ባስተማራቸው
አንበሳ እንደሆነ የሚጠብቃቸው!
አንበሳ እንደሆነ የሚጠብቃቸው!

# ጥሬ ጨው

መስለውኝ ነበረ፤
የበቁ ነየቁ
ያወቁ የረቀቁ
ለካ እነሱ ናቸው፥
ጥሬ ጨው ........ጥሬ ጨው
ጥሬ ጨዋዎች
መፈጨት - መሰለቅ - መደለዝ - መወቀጥ -
መታሸት - መቀየጥ
ገና እሚቀራቸው፤
‹እኔ የለሁበትም!›
ዘወትር ቋንቋቸው።

# አድማሳዊ ፍቅር

ዛሬ ታመመልሽ በትላንት ተለክፎ
አድማሳዊ ፍቅር በእውነታው ጐልድፎ
ድሮውንስ ቢሆን -
ሰማይና ምድር መቼ ተገናኝተው
  መቼ ተሳሳሙ?
ያው እንደኔ እንዳንቺ መስሎት እንጂ ዓለሙ
በምናብ አተያይ በገመት በሕልሙ።
ልብ በይ
አንቺ ሆይ፥ -
የኔና ያንቺው ጠብ አይደለም የርስ በርስ
ይልቅስ እንጂ ነው የራስ ሥጋና ነብስ
ስሜት እሚመትር ደም እሚያበሰብስ
  ከራስ እሚያናክስ።
በዐይነ ጥላ ታስረን
በተራ እሴት ታጥረን
በ«ምን ይሉን» ደክመን፤
ከዚህ የሕይወት ዝፍት
ማኅበራዊ ውርዴ

ምድራዊ አመሳሶ መላቀቁን አጥተን፤
የነብስን ዋይታ
የፍቅርን ኡኡታ
የሐቅን እሪታ መመለስ ካቃተን፤
ለኔዎች ላንቺዎች
ለፍርሃት ልጆች፥
ለፍቅር ጭንጋፎች
ለፀፀት አምራቾች፤
ከዋክብት ይውደቁ
አበቦች ይድረቁ።

# መስከረም

(በድምር - የሴትና የወንድ - ኅብር ድምፅ)
በሰማያዊ መስከረም ሰማይ
የፈነጠቅሽ አብዮት፥ ፀሐይ
ብሩህ - ዕንቁጣጣሽ - ሲሳይ፤
ምን ያህል ዘመን ምዕት ዓመት
ምን ይባል ትግል ምን ጥረት፤
አድኅሮትን ያህል ጨለማ

ጨለማን ያህል ጠላት
ረግጦ በድል ለመምጣት?!
(በነጠላ - የሴት ድምፅ)
 በሉ፥ ማን ያርቅ ቅኔውን
በሉ፥ ማን ያትት ታሪኩን
 የጨለማውን?
(በድምር - የወንድ ድምፅ)
 ያንኮካሸከው ወይ ቅጠሉ፤ ያኈጎድጉደው ወይ አምባው
ያንጐራጉሩት ወይ ወንዞቹ፥ ያጉረምርመው ወይ ተራራው
ዋ ይበልለት አሞራው፥ ያስካካለትው ወይ ጥንብ አንሣው
ይስገምግምለት ወቸገል፥ ያላዝንበት ወይ እንስሳው
ዐዋይ ታቃስተው ይሆን፥ የገደል ማሚቶ ታልቅሰው
ወይስ አድባር ትጨኸው........
(በድምር - የሴት ድምፅ)
 አይሰብረውም ወይም
የያሬድ ዜምና የተክሌን ቅኔ
ይካተታል ወይ
በዘር ያዕቆብ ፍልሥፍናና የዱር ምናኔ
አይዘለውም ወይ
ገደል ስንክሳሩን ተአምር ድርሳኑን

የዓምደጽዮንን ዜና መዋዕሉን
የሳባን ተረት ክብረነገሥቱን
የካህኑን ዮሐንስ ዐይናማ ቃፊት ያን መስተዋቱን
ልፋፈ ጽድቁን ዐውደ ነገሥቱን
የአባ መጣፉን የሺህ ኪታቡን
   አይዘለውም ወይ
(በነጠላ - የወንድ ድምፅ)
ታድያ ማን ያርቅ ቅኔውን
ታድያ ማን ያትት ታሪኩን
   የጨለማውን?
(በነጠላ - የሴት ድምፅ)
   አብዮት - ጽኑ
ዝማሙን የፈታላችሁ ልጓሙን ያነሣላችሁ
ቃል - አንደበት የሰጣችሁ
ብዙኃኑ ተናገሩ ታሪኩ ነው የራሳችሁ
   ቅኔውም ነበር ሕይወታችሁ
(የሕልም እሣት በየበረዶ ጎጆአችሁ)
(በድምር - የሴትና የወንድ ኅብር ድምፅ)
   የጨለማውማ ታሪክ፥ የጨለማውማ ቅኔ
ይፋጃል ከብረት ሰማይ፥ ይጮሃል ከቦምብ ካዳፍኔ

ያልተባል የጭቁን ሐኔ!

ያፍማል የታጋይ ወኔ!

(በጣምራ - የወንድና የሴት ድምፅ)

ጉበዝ፤ -

ከሰሜን ተራሮች አናት አቆልቁለህ አስተውለው

በትዝታ ዐይኖችህ ቃኘው ዙሪያ ገባውን ድፈረው

በሸለቆው በአምባው በደኑ ሆነ በፋልማው

በባድማው በበረሃው በቆላው ሆነ በደጋው

እንደ ጥልማሞት ሲንከላወት

ፊትህን እሚጋርደው በተራቆተ ስብእና

በረከሱ እጆች ተጋልጦ

ዐይንህን እሚጋርጠው የህልውናው ገበና

አንደበቱ እንደ በሬው

ተሸብቦ እምታየው በዝማም ጽኑ ካቴና

ይኸ ጉልቄ መሣፍርት የሌለው ይኸ ሁላ የቀትር ጥላ

የትላንት እኔነቴ

የወዲያ ቀን ማንኔቴ እንጂ እንዳይመስልህ ከቶ ሌላ

ተረት አፈ - ታሪክ ቅጻላ

መንጠልጠያ የአንቃ ባላ

አንዳች ላንቁሶ ከለላ።

ሕሊናህ ይፍረደኝ አመዴ፥ ልቦናህ ይይልኝ ወገኔ

ያ እንደ ነበር የትላንት መልኬ፥ እሱ እንደሁ የነበር እኔ።

ጠኔ የጣላት የወፍ ጫጬት፥ ጭው ጽው ድምፅዋ ነበር ድምፄ

የዘመን እንጉርጉሮዬን የወረሰች፥ የዋኔም ቃሏ ነበር ቃሌ

የምዕተ ዓመታት ነጭ ማተቤ፥ የየዕለት ውሎ መስቀሌ።

ሆዴ ነበር፤

ለአውድማ ያልበቃው ክምር፥ የሻሸረው አዝመራ

ጐኔ ነበር፤

ቦና የበላው ሰብል፥ የቆመው ቀጥኖ ከጭራ

ዐይኔ ነበር፤

የባድማ ዐለት የዐለት ጐተራ

ልቤ ነበር፤

የኸርማ ንፍገት የውሃ አንጡራ

ተፈጥሮና ሰው

ሰውና አድኅኖት ባንድ የፈተሉት ወፈናጅራ

የበጋ ጐርፉ የክረምት ብራ።

(በድምር - የሴትና የወንድ ኅብር ድምፅ)

የጨለማውማ ታሪክ፤ የጨለማውማ ቅኔ

ይፋጃል ከክብረ ሰማይ ይጮሃል ከቦምብ ካዳፍኔ

ያተባል የጭቁን ሐኔ!

ያፍማል የታጋይ ወኔ!

(በድርቡ - የሴትና የወንድ ድምፅ)

የእግዜር ቤተሰቦች፥

ጉልተኛ ዕጨጌዎች መኳንንት መሣፍንት ነገሥተ ነገሥታት

ልዑል እምልዑላን ክቡር እምክቡራት፥ ቅዱስ እምቅዱሳት

ብፁዕ ወብፁዓት ጳሐፌ ትዕዛዝ

(የጨለማ ልጆች)

ታገለህና ደምተህ

ያለመለምከውን የታሪክ ባንዲራ የነጻነት ዓርማ

የወዝህን ሰንደቅ የክንድህን ግርማ

ተጠየቅ ታውቃለህ!

ነጥቀው እንዳደኸዩህ በፊውዳል ዘመናት

በዚያ በጨለማ!

(በድምር - የብዙኃኑ ድምፅ)

አለ እንጂ የከፋ ከዚህም የባሰ

ታሪክ ሲቋረሱ ገደል ሲዛረፉ ተርፎ ከራሳቸው

ከሰማዕታት ሳይቀር ከመላዕክት እንኳን አሉ የደረሳቸው!

በዐድዋ ጦር ሜዳ በዚያ ቀውጢ ሰዓት ሕዝበ ዓለም ሲዋቃ

አይደለሞይ ጊዮርጊስ፥ ጊዮርጊስ ሰማዕቱ ለታሪክ የበቃ!

የሮሀ መቅደሶች

ዝነኛ ሕንፃዎች ከዐለት ማኅፀን ተፈልፍለው የወጡ
ነው አሉ በመላዕክት ከአርያም ወርደው በሌሊት በመጡ!!
ወገኔ አስተውለው፤
    እኛን የኩሽ ሕዝቦች የሴምም ወገኖች
    የጠይሟን አፈር ጠያይም ትውልዶች
ቸሄ - አይመለሌ፥ መንዜ - አንኮበሬ፥ ዶርዜ - ወላይታ
    ሐማሴን - ኢጋሜ፥ ቦረና - ወለጌ፥ ሐድያ - ከንባታ
አገዌ - ቢለኔ፥ ጀበርቲ - ኡጋዴ፥ ሣሆእ - አሣውርታ፥
እስላም ክርስቲያን፥ አረሚ ፈላሻ
    ‹ጥንበ - በል ተልካሻ›፥
ብለው በመደንበር በቀጫጭን መስመር
በቋንቋ - በሃይማኖት - በወንዝ - በመንደር
የአንድነት ግንባችን በማፈራረስ በመሰነጣጠቅ
ለስንት ዘመናት
የጨለማ ልጆች በፍራሻችን ላይ ካቡበት ሠቀሠቅ?!
(ድርብ - የወንድና የሴት ድምፅ)
ያገሬ አርሶ አደር ያገሬ ወታደር ያገሬ ወዛደር
የሰፊው ሕዝብ ስፍር የብዙኃን ድምር
ለደቂቃ ቁራጭ ለቁራጯ ቅጽበት ለቅጽበቷ ከፋይ
ከቶ ፀሐይ ሳታይ፥

በዚያ በጨለማ ታጥረህ ስትሠቃይ፤
ይታወስህ ወገኔ
የጉልተኛ ልሣን የከበርቴ አንደበት በልፍኝ ባደባባይ
ያወራ አንድ ነበር ሀገርህ እንደ ሆነች የዐሥራ ሦስት ወር ፀሐይ።
(በድምር - የብዙኃን ድምፅ)
በወዜ በደሜ
ሀገሬን ነኝ እኔ፥ እኔና ናት ሀገሬ
ጦርነት - ሰላሜ፥ ጤንነት - ሕመሜ - ደስታ -ችግሬ
ደሳሳ ጐጆዬ የቀሳ ትዳሬ።
ላፍ አይገድምና ባላባት ከበርቴ
እልፍኙን ከሆነ ብሩህ አደባባዩን ሀገሬ ማለቱ
እንደ ዶግ ተማግደን
እንደ ጧፍ ተቃጠልን
ሰጥተነዋልና የሐሴት አምኃ የላቀ ጉልበቴ
አልበለም ከቶ፥ አምኗል ባንደበቱ።
አለበለዚያ ግን ባሰት ተጠቅሳለች ሀገሬ ምድሪቱ
ያው እንደ ባህሉ
የባላባት ተረት የከበርቴ ወጉ ተጋኗል ኩሸቱ።
ማልዶ ወከናፉ ማልዶ ከመጫኛ ማልዶ ከሞተሩ
ማልዶ ከዋግንቦው ማልዶ ከምድጃው ማልዶ ከቀንበሩ

ሀገሬ - እኔነት ጨለማ ትዳሩ፥ ጨለማ አጥሩ።

የጐጆው ጉልላት

የየሸከላ ክፉይ ላንድ አፍታ አይዘንጋ ይታወቅ ምሥጢሩ።

ወገኔ እየውማ፥

በወንዟ ሳንደረጅ በአፈሯ ሳንወዛ በአየሯ ሳንለማ

በጉልበተኛ ኮቴ ዘወትር ስንረገጥ ዘወትር ስንደማ

በሲሶ በእርቦ ሥጋችን ሲዳቀቅ ቀልባችን ሲዘራ

በከበርቴ ገብያ አንሶ ሲመነዘር ወዛችን አንጡራ

ምን ትባሏ ፀሐይ

ምን የሚሏት ብርሃን አንዲት ዘሃ ጮራ

ከኛይቱ ጐጆ ከደሳሳ ቀሳ ገባች በወር ተራ?!

(በድርብ - ወንድና ሴት ድምፅ)

እንደዚህ ከተዋጥህ በትዝታ ዜማ በእንጉርጉሮ ቃና

በዐይኖችህ እያለፈ ጠፋ ሕይወት ባድማ ያ ሁል መርግ ጫና

እንደምን ነበረ?

እንዲያ ስቡር ቅስምህ እንደገና የቀና ደሞ የተንሠራራ

ተፍታቶ አንደበትህ አብዮትን ያህል ፈራጅ ዳኛ የጠራ?

(በድምር - የብዙኃን ድምፅ)

የአብዛኛው ሕይወቴን የጨለማ ታሪክ ቀድመህ ብትጠይቀኝ

እንደ ረዥም ዕድሜው ደሞ እንደ ትልቀት አጥብቆ እየያዘን

አስቆዘመኝ እንጂ፤ - ብርሃንማ ምዕራፍ ሌላም ታሪክ አለኝ።
ሌላም ታሪክ አለኝ፤ ያልጣለው ጨለማ ወይ ቀቢፀ ተስፋ
በእግረ ሙቁ መጥበቅ በቀንበሩ መክበድ አንገቴም ቢደፋ።
ቅንጣት የብርሃን ዘር፥
በልቤ አጐንቁሎ ዝግ ብሎ ሥር ሰዶ እያደር የፋፋ።
እንደ አንዲት ምስኪስ ሴት
እንደ በኸር ወላድ ምጥ እሚያስቅስታት ለሞት የቀረበ፥
ማንስ አለ እንደሷ
ከጨለማ ወጥቶ ሕይወትን ለማየት ሕይወትን ለማቀፍ
ልቦናው የጓጓ መንፈሱ የተራበ?
እንደዚሁ ነበር የእኔውም ተጋድሎ የእኔውም ተጋትሮ
ዐምጦና ቆስሎ ደምቶና ገርጥቶ ከስሎ ተኮማትሮ
የቅንጣቲቱን ዘር የዘሪቱን ቅንጣት መታደግ ጠንክሮ
ሕይወትን ማለምለም ያንን የሞት ኬላ ገነጣጥሎ ሰብሮ።
ከበባው ሲበዛ
ብዝበዝው ሲንዛዛ
ከጨለማው ጥጋት በውስጤ የበቀለች ያቺን ዘሃ ብርሃን
አራግቤያታለሁ
ዙሪያዬን ጨለማ ቀጥቼባታለሁ
የፋኖ ፋናዬም ሁና አይቻለሁ።

በጉራዕ ዶጋዓሊ በኲዓቲት መተማ በታላቁም ዐድዋ

በኡጋዴን በማይጨው በሌላውም ሁሉ ያገሬ ክልልዋ

ያችው ወሰው ብርሃን

ባሳደረችብ ሰብዓዊ ጀግንነት የደረጀ ወኔ እምነትና አለኝታ

ስደከም ስበረታ፥ ስወድቅም አንሥታ

ሰው - በል ጅርማንጅር

ድንበር - ሰበር መንጋ ደመ - ሰች ተኩላ

በቀጭኑ ክንዴ

ተመቶ ተጥሏል በየፈፋው ቀርቷል በየአሸዋው ሁላ።

ወገኔ ዘመዴ፤

ያችው ቅንጣት ብርሃን ስንት መንገድ መቷት አንጋዳ ረባዳ

በየስንቱ ምዕራፍ በጉም ተጨፍቃ በጭጋግ ተጋርዳ

ግን ሁልጊዜም የትም ከሕልሜ ተሻሽታ ከወኤ ጠጥታ

በኔዎች ለኔዎች አብባና አሽታ

እነሆ በቃነ

በዑይናችን ለማየት ደምቃና ተፍካክታ

ቷ ብላ፥ ፈንድታ።

ከዛሬውን ደረሰች ፍሬዋን ልታድል ከረጢቷን ፈትታ

የሰላምን ዋጋ - የእውነትን ዋጋ - የዕሪናን ዋጋ

ልትሰብክ ልታስተምር ለሰው ልጅ በተርታ

ብራና ያላየው ያልነካው
ቀለም ያልዳሰሰው
ሓቀኛ ታሪኳን፥ ዜና ገድሏን ከፍታ ጉባዔ ዘርግታ።
(በነጠላ - የሴትና የወንድ ድምፅ)
ያገሬ ሠርቶ አደር
    ታሪክህ ነው ቅኔ ቅኔህ ነው ታሪክ
    እልባት የሌለው መጠን ወይም ልክ፤
ያም ሆኖ ተቋጨ
በመስከረም ፀሐይ በአብዮት ብሥራት ዜና
የጭለማ ልጆች ታዩ ተገላልጠው በዕርቃን ገመና
ምፅዓት - ትንሣኤ
ዳግም ላይኖራቸው ቢወዱም ባይወዱ
ከወንበርህ ቀርበው ተፈጥመው ሔዱ።
(በድምር - የብዙኃን ድምፅ)
በሰማያዊ መስከረም ሰማይ
የፈነጠቅሽ አብዮት ፀሐይ
ሉል - ዕንቁጣጣሽ - ሲሳይ
ምን ያህል ዘመን ምዕት ዓመት
ምን ይባል ትግል ምን ጥረት፥
ፊውዳሊዝምን ያህል ጨለማ

ጨለማን ያህል ጠላት
ገድሎ በድል ለመምጣት?
(በነጠላ - የሴት ድምፅ)
መስከረም
የብዙሃን ብሩህ ሰማይ
ግዙፍ ደማቅ አደባባይ
አብዮት ዕንቁጣጣሽ - ሲሳይ
ይዘምሩ ዕፅዋትሽ
ይምነሽነሹ ጽጌያትሽ
ከበሮ ይምቱ አምባዎችሽ
ድላቸው ነውና ድልሽ።
ገድላቸው ነውና ገድልሽ።
(በነጠላ - የወንድ ድምፅ)
መስከረም፥
የአዲስ ልደት ውብ ብራና
የትግል ደመራ ደማቅ ፋና
በአድማሳትሽ ላይ ተግ አለ
ሠፈነ ቀስተ ደመና
የሰውና ሰው ኪዳን ዜና።
እልል ይበል ሠርቶ አደርሽ

እሰይ ይበል ብዙኃንሽ

ሕልሙ ነውና ሕልምሽ

ግቡ ነውና ግብሽ።

(ድርብ - የሴትና የወንድ ድምፅ)

መስከረም

የጭቆን ሕዝብ የቀኑ ቀን

የዘመን ትግሉ ሰመመን

የየዕለት ድሉ የየዓመት ተመን፤

የከርሞሽም ድል ቡቃያ

እንዲበቅል ከዛሬ ጉያ

ወጣት ልጆችሽ ብቅ ይበሉ

ለስምሽ እንግጫ ይንቀሉ

ለክብርሽ አበባ ቀጥፈው።

ቃልሽን ቃላቸው ይጣፈው።

እንደበታቸው ይዘምረው።

(በኅብረት - የወጣት ሴቶች ድምፅ)

አበባዬ ሆይ - ለምለም

አበባዬ ሆይ - ለምለም

አብዮት - ለምለም

መስከረም - ለምለም

እንዳንቺ ቆንጆ የለም።

ባልንጀሮቼ - ቁሙ በአንድነት ቁሙ በተራ

አድኅሮት ወድቆ - ቤት እስክሠራ

ዋልጌነት ቀርቶ - ቤት እስክሠራ

መሃይምነት፣ ድኅነት ጠፍቶ - ቤት እስክሠራ

በሽታ ሞቶ ቤት እስክሠራ፤

እሠራለሁኝ - ከቤትም ቤት

ሐቅ ዲሞክራሲ - የመላበት፤

እሠራለሁኝ - ከቤትም ቤት

ሠርቶ አደሮቼ - ‹ሚኖሩበት›፥

እሠራለሁኝ - ከቤትም ቤት

ዕውቀት አዱኛ - ‹ከሚገባበት›፥

እሠራለሁ - ከቤት ቤት

ቅኔና ዜማ - ‹የሚሠፍንበት......ወዘተ

አበባ ለምለም

መስከረም ለምለም

አብዮት ለምለም

እንዳንቺ ቆንጆ የለም.....ወዘተ

======

1973 (ይህ ግጥም ሁለተኛውን የኢሠፓአኮ ጠቅላላ ጉባኤ አስመልክቶ በተዘጋጀው የኪነጥበብ ውድድር፥ በሥነ ግጥም ዘርፍ አንደኛ የወጣ ነው። መዘከርነቱም ለሀገሬ ቆራጥ አብዮታውያን ይሁንልኝ።)

## በስሙ ሠየማት

መቁጠሩንስ ቆጥሯል የትግል አቡጊዳ

በደሙ እየጻፈ የሕይወት ሠሌዳ

ላያሌ ዓመታት ለረዥም ዘመናት

ጨሶ እንደ ርጥብ እንጨት ተቀጣጥሎ እንደ እሳት

እንደ ወዙ ልቡን ሳይገብር ለጠላት።

መቁጠሩንስ ቆጥሯል፥ .......

ቸል ብሏት አያውቅም

የሕይወትን ፊደ ዳር ሁኖ ዳር ቁሞ

ቃል ኪዳን ነበረው በራሱ ጉባኤ ምሎ ተፈጥሞ

የራሱ ሊያደርጋት ወድቆና ተነስቶ ሮጦና አዝግሞ።

ቃል ኪዳን ነበረው፥

የሕይወትን ፊደል ቅንጣትና ዘሯን

እጅግ ለምለም ቡጧን፤

በመንቆር ጣቶቹ ሰቅሶና አፍኖ

የያዛትን ምስጡን ትሉን ትላትሉን
ከላይዋ አራግፎ አብኖ አትኖ
በወዙ ሊያፋፋት
በአምሳሉ ሊቀርፃት እንዲኖራት መቅኖ፤
እንዲኖራት ጤና ሰላም ብልጽግና
የማይታጠፍ ሰንደ ከቶ እማይገሥ አርማ
        የእምነት ዕፁብ ፋና።
እነሆም አልቀረ፥
ቃል ኪዳን ቃል ሁኖ አየነው ሲለማ
ከጨለማ ልጆች ከምስጣምስጥ ትልቾ ብርሃንን ሲቀማ
ልትግሉም መዘከር ለድሉ ዋስትና
ለዛች የሕይወት ፊደል
ለዛች የፊደል ዘር
ለዛች የዕውቀት ፍሬ ሐውልት ቀረፀና
እውነትን ውበትን ፍቅርን አርነትን በላይዋ ነደፈ
በስሙም ሠየማት፥
በብሩህ ደም - ቀለም «ሠርቶ አደር» ሲል ጻፈ።

# <u>ምነዋ ባየሁኝ</u>

ምነዋ ባየሁኝ!

መሬቷን ሰቅስቄ

ዛፏን ተራራዋን ቤቷን ሰዋን ሁሉ

አንድ ላይ ጠቅልዬ

(በብርሃን ፍጠንት በሚያዘገዝግ ዘንግ)

ወዲያ አንጠልጥዬ

ከሰማያት ጣራ ገፍቼ ሰቅዬ፣

ምነዋ ባየሁኝ!

ጠፈሩን አንጥፌ

ጓዙን ከዋክብቱን እግሬ ሥር አርግፌ

ቀስተ ደመናውን ፈትቼ በጃቼ

በቀለማት ምሥጢር ተደመው ዐይኖቼ፤

ምነዋ ባየሁኝ!

ምነዋ ባየሁኝ!

የሩቁን አቅርቤ

የቅርቤን አርቄ፥

ጨረቃን ሰልችታኝ

ምድሪቱን ናፍቄ።

## ጋዜጣው

ጋዜጠኛው አባ ጆፌ፤

ኸሯው ሸዌ - ብር ክንፌ
ካደባባይ እስከ ጓዳ
ከአውላላ እስካንጋዳ
ከቁር ሐሩር - ከለም ጠፉ
ከሸለቆው ከአፋፉ
ከደፍ ጠረፍ - ከች ከተፉ!
ጋዜጠኛው አባ ዲና፤
በሺ እግሮች እምትዛክር
በሺ ዐይኖች እምትማትር
ማን እንዳንተ - የትም ደራሽ
ምዕራፍ ገሣሽ - ኬላ ደምሳሽ
ከነገር ነገር - ነገር ጨራሽ
ከውጥን ውጥን - ግቡን አሳሽ፤
ማን እንዳንተ?

   ስንቱን በዐይኑ የሸለተ
   በትዕዝብቱ  የሞገተ
   ማን እንዳንተ?......

ገና ቀርበህ ሳትጨብጠው
ለዐመል ያህል በቃኘኸው
በሩቅ ድምፅህ ‹ሚበረየው

ሲቃ ይዞት እሚርደው፤

ግንባርህን እሚፈራ

የኪክራሲ - የቢግራሲ

አባ አድኃሪ - አባ ሴራ

ምን ያህል ነው

በብዕርህ የከተብከው?......

ጋዜጠኛው አባ ጆፌ፥

መንቆር ብእርህ ስል ነው ካራ

‹ሚጐደፍር የአሻጥር የዕድፍ ጋራ

እሚፈታ የአድኃሪን መንጋ ጐራ፤

እስክትወጣ እውነት ብፅዓት

አንዲት ቅንጣት - እውነት ብሥራት

ቁሻሻውን ጥራጊውን

   በታተነኸው እንድ እዘሃ

ስንቱን እንከን

   ትነቅሳለህ

ስንቱ ሰሀ ፡

በር ቢዘጉ አይመልሱህ

አትቀየም ፊት ቢነሡህ

በመርፌ ዐይን - ሰተት ውልብ

በስቁረቷ - እልም ስልብ
ይቺን ጡልብ - ከዚያች ገፈፍ።
መሠሪ እጇን ሲቃጣብህ
አሉባልታ ሲዘርፍብህ
እምትዳኘው ሲዘርፍብህ
እምትዳኘው በትዕግሥትህ
በኮክቴል ላይ ሲጮህብህ
ባንድ ጉንጭህ
    ዐረቄዋን - ሳብ ምጥጥ
በሌላው
    ቁም ነገሯን - ዋጥ ስልቅጥ።
ዐይኖችህ የጊዜ ዐይኖች
ዝንተ ዓለም ክፍት ግዙፍ በሮች
ጆሮዎችህ እንደ አንቴና
የከበሮ ስራ ብራና፥
ጋዜጠኛው፤.......
1974 (እውነትን ለሚፈልጉ ንቁ ጋዜጠኞች)

# ትዝታ - ከበሮ

ተንተርክኮ እሳቱ ነበልባሉ አብቦ

ኑ ደርቡት ሲለን ጃዌውን አቅርቦ
የኔና ያንቺ ልብ ሙቀት - ከላ ኖሮ፣
ይኸው የተረፈን፡ -
ቁርና እንጉርጉሮ፥ ዐመድና እሮሮ
ምቱ ውል የሌለው ትዝታ - ከበሮ።

# ፍቅርና ተግባር (አንድ ቅንጣት አበባ)

ስንቱ ነገር ቀርቶ -
ውበት ደግነትሽ ትዝታው አፍጅቶ
ደርቆና ገርጥቶ
በጥላቻ ደለል
በቅያሜ ዳዋ እያደር ተበልቶ
እያደር ገርጥቶ
አንድ ነገር ብቻ
አለ አንድ ነገር ከኔ ዘንድ የቀረ
ባይኖቼ ማዕዘን እንባ እያስቋጠረ
በሩቅ ዘመን ልቤ ዛሬን እየዋለ
ዛሬን እያደረ።

በዚያች መጢቅ ሰዓት፡ - ስሜታችን ባብቶ በፍቅር እምቢልታ

በተግባሬም ጥሪ መለከት ግምግምታ

አንቺና ግዳጄ

ግዳጄና አንቺ ክፍላችሁት ልቤን

ሁለት ሁለት ቦታ፤

በዚያ መስቀለኛ መንገድ ላይ እድነ ቆምሁ

ሳስብ ሳመነታ፤

ቀጥፈሽ የሰጠሽኝ

በለጋ ጣቶችሽ ያች ቅንጣት አበባ

በተግባሬ አለኝታ በግዳጄ ተስፋ

ፍሬ እንድገነባ

ከቶ አትረሳኝም በክረምት በበጋ

በነጋ በጠባ።

ለካስ አይደለችም

ቅንጣቲቱ አበባ

ጠፊና ረጋፊ የቅጠል ወለባ፥

የዛሬ ውበት ድምቀት

ግን የከርሞ ትቢያ የነገ ገለባ።

ይልቅስ ሕያው ናት

አንዳች የፍቅር ዐዋይ የተግባር ጥሪትሽ

ከቶ እማትሚሽሽ
በልቤ የጻደቀች ቋሚ ሐውልትሽ
ለወገኔ ፍሬ ላንች መታሰቢያሽ።

# ኦይ ጆኒ ኦይ ጆሊ

ኦይ ጆኒ ኦይ ጆሊ
የገበያው ችምት፥ የቤተክስያን ጡሊ
ብዥ ቅዝዝ በአራዳ፥ ፍዝ ድንግዝ በሜዳ
ሽር ብር በማጀት፣ ሽው እልም በጓዳ
ውትርትር በአውላላ፥ ፍስ እብስ ባንጋዳ
ብቅ ጥልቅ
ጥልቅ ብቅ በጉም ጭጋግ አምባ
አየሩን ሰንጥቆ -
አሜሪካን ሊደርስ አውሮፓ ሊገባ
(ከብሔረ አፍርንጅ)
በሐበሻ ምድር ዘመን እርም ብሎ
እዚያ ጡት ሊጣባ!
ኦይ ጆኒ ኦይ ጆሊ

ሰው ለምን ያማዋል?
ባህል አፍራሽ ብሎ ይህን ጆሊ ጆኒ
ቅጠል በልቶ እሚውል
ዕፅ አሽቶ እሚያድር እሱ እንደሁ መናኒ
　　አባ ሆይ ተብዬ
ልከበር አላለ አልተመጻደቀ
　　‹ስምዓኒ› እያለ
ጧት ማታ በስግደት ቅስሙ እየደቀቀ
　　　　ወገቡ እያለቀ።
አይ ጆኒ አይ ጆሊ
ዕድሩን ርቆ
ውጣ ውረዱን ንቆ ሲገባ ሱባዔ
　　　　ከብቻ ጉባዔ
ይታየዋል ዓለም
ሥያሜ ያላገኘ ያላወቀው ካርታ
ኅብሩ የተለየ
ከምድራችን ባህል ልምድና ገመታ፤ -
ጽጌረዳ ኸርማ ወርቅማ ጭልፊቶች
　　　　ሰማያዊ ላሞች
ክንፍ አልባ አናስር፥ ጥርስ አልባ ዝሆኖች

ተንፏቃቂ አዕዋፍ፣ በራሪ ኤሊዎች
ቀንዳቸው የሾላ ገጸ ሰብእ ፍጡሮች
በዐይናቸው እሚበሉ የጠይብ ዝርዮች
ውሉደ አሣማዎች
ይታየዋል ዓለም፤......
ብሔረ አንክሮ የድማሜ ጉራ
ፍቅር የሚያሼትበት ቀድሞ ሳይዘራ
ባንድ እሚውሉበት
እባብ ከእርግብ ጫጩት ከሲላ
ኩታራ ከገዲ አባግዕ ከተኩላ።
ሌላ አለ ብዙ እሚገለጽ ለሱ
እሚሰማው እሱ
እንደ ባዕድ አካል
ተገንጥሎ ሲሔድ ራሱ ከራሱ
እጆቹ እያጠሩ
አቅቶት ሲቸገር መዳበስ ማበሱ
እያደገ ሒዶ
የገዛ አፍንጫው ይላጋል ከአድማሱ!
ወንዙን ገመገሙን
እመር ብለው ሲያፍሉ ዳንዴዎቹ እግሮቹ

ላንዷት ቀጭን ቦይ ግን
ይጨነቅ መንፈሱ ይተሣሠር ወርቹ፤
እየተለጠጠ
ደግሞ እየገዘፈ ጡንቻው የደረቱ
ይዘጋል ትራፊክ
የመኪና መንጋ ያቆማል ከአስፋልቱ፤
ጆሮው እየሰላ ይሰማዋ ጐልቶ
የነብሳት ሲጥሲጥታ
የጣዝማ ኩርፍታ
በሣጥን ውስጥ ያለ.....
የሸማኖ የብል ፍልሚያና ቱማታ፤
ደግሞም በሰማይ ቤት....
የመላእክቱና የአጋንንቱ ተረብ አሽኮለሌ ቧልታ
አየሩን የመላው
የጸጥታው ጩኸት የጩኸቱ ጸጥታ።
ሲታገል ይታያል
በየሲጃውራው ጭስ
በየጭሱ ክቦሽ በመርፌ ቀዳዳ
አሾልኮ ራሱን ለመሮጥ ሲዳዳ፤
ምላሱ ያጣጥማል

ጥርሶቹ ያደቃሉ የነፍስ ጭብጦ
ይክባል ተራራ
ያፈርሳል ተራራ በቅጽበት ተመስጦ
    በዕፀ ፋርስ ፈረስ
አንዴ ከጋለበ ከሔደ ሽምጦ።
    አይ ጆኒ አይ ጆሊ
ይጋልብ እንጂ ታዲያ
በዕፀ ፋርስ ፈረስ እንዳሻው ተቀምጦ
አለበት በተራው፥
ኮርቻ ደልድሎ እሚጋልብበት ወገቡን አጉብጦ
አንዳች የዛር ውላጅ
    (እስከስሙ ዱካክ)
‹ምሴን ምሴን› እሚል ዐይኑን አስፈጥጦ
    ዐረፋ አስደፍቆ
ቀልቡ አስጠፍቶ ቅስሙን አደፈጣጦ።
ሚሚ - ቲቲ - ጁሊ፥ አኒ - ቤቲ - ሱዚ
    ጠይሚቱ ሮዚ
    የዘመኑ ጻድቃን
ጊዜያቸውን ቸረው ልባቸውን ሰጥተው
በዲስኮ ደስቀው በሮኩ ተራኩተው

በብሉስ ለስልሰው........ለስልሰው......ለስልሰው

ከደረታቸው ውስጥ -

በትረሎሚ አውጥተው - አውጥተው - አውጥተው

አውጥተው - አውጥተው

በእጆቹ አስጨፍልቀው በድዱ አስጨምቀው

ካላስተናገዱት ወይ ካላባበሉት፤

ከቶም በጄ አይል

ከቶም አይባበል ጆኒ ከመግፈፉ፤

ይበልጥ ከማሣቀቅ ወይ ከማስጨነቁ

እሱ እሳት ጉርሶ

የኮሾ ሲጃራ እንቅብ ሙሉ ዐመድ

ቁልቁል በጉሮሮው መሸቅሸቅ ማጨቁ!

ጆኒ ነው ጋላቢ - ተጋላቢ ጌኛ

ጆኒ ምስኪን ፈረስ - ብርቱ ፈረሰኛ

የት ይሆን ድንበርህ

የመድረሻህ አቅጣጫ?

የግልቢያህ አድማሱ፥ የጉዞህ መቁረጫ?

# ያቺ ማች ቀን

ጊዜ ሆይ

ሕያው ጊዜ ሆይ
በማይሞተው ገጽህ ላይ
የወጣችን ያቺን ቀን
ያቺን -
የነቀርሳ እባጭ መሳይ
የመርዝ ከረጢት ሥራይ
ሥሯን በርብረህ ንቀል
ዕጢዋን ፈልገህ ግደል።
ትብነን
ምትክ አይኑራት አምሣያ፤
ትምከን
ወራሽ አይኑራት ዝርያ፤
የሰውን ልጅ ብሩህ ጉዞ
የሰውን ልጅ ደማቅ ዕጣ
በጥላዋ ሳታዳምን፥ በግንባሯ ሳታነጣ።
በሽሏ ሳትቀጭ ቀርታ
ሰፍታ ከሔደች ደርጅታ
ከፅንሷ ሳትወድቅ ተመታ
ገዝፋ ከመጣች ጕልብታ፤
የሰዎችን ሕሊና አንቃ

በአንጋቦስ እጆች ፈጥርቃ
እኩይ ትዝታን አንቅታ
ትላንት እትራቱን ከፍታ
የተኙ ትሎች አህውይታ
የሰውን ልጅ አንድ ተስፋ አንድ አለኝታ
በቅዠት እንዳትይዘው ተስፋፍታ።
በቅዠት እንዳትይዘው
በቡከንሸልድ መሰል ጐራ
በኦዝቪትዝ እልፍ ኤኪራ።
ጊዜ ሆይ
ሕያው ጊዜ ሆይ
በሻቲላና በሳብራ
የወጣችውን ጨረር ፍራ፤
እንደሷም ጽልመት የለ
ብርሃን ተመስሎ ብርሃንን ያከሰለ።
1976 ( በሣብራና በሻቲላ ለወደቁ ፍልስጥኤማውያን።)

# ጉዟችን

ሩቅ ነው ጉዟችን፤......
ከቶ እማይመጠን

በሚትሮች ጥቅል በአምባዎች ድምር
    በኬላዎች ቁጥር፤
አጣርሶ እሚያልፍ ነው
የዘመንን ቀመር የጊዜንም ስፍር፣
አቋርጦ እሚሔድ ነው
የራስን ማንነት ስብእናም ጭምር።
ድንቅም ነው ጉዟችን፤
ከኛው እሚጀምር
በኛው እሚጀምር ሃሌታ ምዕራፉ
ከወገን እስኪዘልቅ ከትልማችን ጫፉ።
ከዓቢይ ግብ - ጠረፉ።
ውል - አልቦ ሕይወትን መሣይ አሜከላ
ንፉግ አተያይን የመሰለ አሽከላ
    እኛው ከእኛው
በእኛው ተመላልሶ ሳንነቅል ሳንከላ፤
ትልቁ ጉዟችን ከቶ አይሠምርምና
    ምን አይፈይድና
እኛው ነን መንገዱ የመነሻው ኬላ።
ይህ ፍቱን ጉዟችን
ቀርጾና አዘጋጅቶን በብርቱ ስብእና

በደደረ ፍቃድ በብሩህ ልቦና

አግዝፎ ያሳየናል

የሕዝብን ሙስና

የወገን ድቀቱን መከራ ፈተና

በጫንቃው የወደቀን ተፈጥሮአዊ ጫና

የስንት ምዕታቱን የበከ ሕይወት ዳና።

አቅርቦ ያሳየናል

ትግላችን - ስፋቱን

ተስፋችን - ጥልቀቱን

የታሪክን ዳፈን የመከፈሉን ክብደት

ክብር መሥዋዕትነት።

ቃልም ያስገባናል -

እጃችንን ጭኖ ከአልባሌ ቀሣ

ረኃብ ድንቁርና ሌላም ሁሉ አበሳ

በወገን ላይ ላይገን ኬህ ከቶ ላይደራ

በእጅና በአዕምሮ

ሊመተር ሊቆረጥ - በትግል በሥራ።

የየወቅቱን አድማስ ያልፋል ዘመቻችን

ሩቅ ነው ጉዟችን፤

አንድም በማለዳ አንድም በበግለግ

አንድም በተጥለግለግ

በዋዕይ በበረድ፥ ወይም በጀገጀግ፥

ግን መቼም - በየትም

በአብዮታዊ ኮከብ በሕዝባዊ ፈለግ

በሀገር ፍቅር ሐረግ

በድል ፍኖት ጠገግ፤፣......


ሩቅ ነው ጉዟችን

ድንቅም ነው ጉዟችን።

ሐምሌ 1977 (ከከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች፤ በመልሶ ማቋቋም ዘመቻ ላይ ተሠማርተው ለነበሩ ምሁራን።)

# እንደግ እንደ ዛፍ

ጥቁር አፈር ዐቅፎን
ጥቁር ብርሃን ውጦን
ሥራ ሥር አንቁለን
 አዝምተን እንደ ሐረግ
ውስጡን ዕመቃቱን
 ጉራንጉሩን ጠገግ፤
ጭረንና አሽተን
 እንደ ፋኖ ሶለግ፤
እንንቀስ አልሚውን
አንልቀም መልካሙን
 እንደ ልባም ሰው ወግ።
ከፍ ብለን እንድናኝ
 አየሩን ልንመላ
ወደ ፊት ለመሮጥ እንሒድ ወደ ኋላ
እንደግ እንደ ዛፍ ዋርካ እንሁን ሾላ።



# ስለደራሲው በጥቂቱ

በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ይርጋዓለም ከተማ ሐምሌ 5 ቀን በ1942 ዓ.ም. ተወለዱ:: የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የርጋለም ከተማ በሚገኘው በራስ ደስታ ትምህርት ቤት የተማሩ ሲሆን ሁለተኛ ደረጃን በኮከበ ፅባሕ አዲስ አበባ ውስጥ ተከታትለዋል። የከፍተኛ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመከታተል በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ የመጀመሪያ፣ በእንግሊዝኛ ሥነ ጽሑፍ ደግሞ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል::

በአጫጭር ድርሰት በግጥምና በቴያትር እንዲሁም በሂስ ሥራቸው በብዙዎች ዘንድ የሚታወቁት ደበበ ሰይፉ የሀገሪቱ የሥነ ጽሑፍ እድገት ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ ጥረት ያደረጉ ምሁር ነበሩ:: በ1966 ዓ.ም. "ሣይቋጠር ሲተረተር" የሚል ድራማ ጽፈው በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ታይቷል::

"የብርሃን ፍቅር" በሚል ርዕስ ያሳተሙት ቁጥር 1 እና ቁጥር 2 የግጥም ስብስብ መጻሕፍታቸው ብዙዎች ዘንድ አድናቆት አትርፈዋል።

**ምንጭ:** የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ለሚሊኒየም ያሳተመው አጀንዳ።

## የደራሲው ሥራዎች

1. የብርሃን ፍቅር (**ግጥምና ቅኔ**)
2. ለራስ የተፃፈ ደብዳቤ (**ግጥምና ቅኔ**)
3. ከባሕር የወጣ ዓሣ (**ተውኔት**)

“ . . . ይህ ቅጽ የኢሰፓአኮን ድምፅ የሥነ ግጥም መድረኮችን ሲሶ ያህል የያዘ ነው ። ከእነዚህ ሲሶ ያህሉ ደግሞ ፣ ገሚሶቹ በቅድመ-አብዮት የተጻፉ ናቸው ። ቅድመ-አብዮት የልጅነት ግጥሞቼ ፣ ድኅረ-አብዮት የጉልማሳ ግጥሞቼ ፣ ባያሌው እዚው እንደ መሆናቸው በሥራዬ ፣ በጅምሩ ለንድፋቸው አልፈለኩም ፣ በድምሩ ሊዘሳቸው ። ስለዚህም ነው ፣ ጎትመት ፋናወጊ ሁናቸው ፣ ወደ እናት ውድ እንግባቢዎቼ ስሽናቸው ፣ በክብሮቻቸውን እንደ ጠበቁ እምታገኟቸው . . . ”

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

ዋጋው ብር 2.25